# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 133 ጥር 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡ በረሀን ታደሰ

## “ኢትዮጵያ በተገቢው ዲፕሎማሲና በሰጥቶ መቀበል መርሕ የባሕር በር የማግኘት መብት አላት”

- ኢንጂነር ስለሺ በቀለ (ዶ/ር)
በአሜሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- “ኢትዮጵያ በተገቢው የዲፕሎማሲ መንገድና በሰጥቶ መቀበል መርሕ የባሕር በር የማግኘት መብት አላት ሲሉ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደርና በዓባይ ግድብ የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድን መሪ ኢንጂነር ስለሺ በቀለ (ዶ/ር) ተናገሩ።

አምባሳደር ኢንጂነር ስለሺ በቀለ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ፍላጎት የማንንም አካል የማይጎዳና በሰጥቶ መቀበል መርሕ የተቃኘ ነው፡፡

«ኢትዮጵያ በተገቢው... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









## «ኢትዮጵያ ዲፕሎማሲዋን ከወገንተኝነት በራቀ መልኩ ያከናወነችበት መንገድ አስተማሪ ነው»

- አንተነህ ጌታቸው (ዶ/ር)
በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የኤዥያና ፓስፊክ ዋና ዳይሬክተር



**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በዘመናት ቅብብሎሽ ከወገንተኝነት ይልቅ ብሔራዊ ጥቅምን በማስከበር ላይ አተኩራ ዲፕሎማሲዋን ያከናወነችበት መንገድ የሚደነቅና ለሌሎችም ተምሳሌት የሚሆን ነው ሲሉ በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የኤዥያና ፓስፊክ ሀገራት ዋና ዳይሬክተርና ከፍተኛ ተመራማሪ አንተነህ ጌታቸው(ዶ/ር)ገለጹ።


አንተነህ ጌታቸው (ዶ/ር) በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመንግሥታት ቅብብሎሽ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከወገንተኝነት ይልቅ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያተኮረ ነው።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ መርሕ ማንንም ወገን የማይደግፍ (Non-Aligned) በመሆኑ በተለያዩ ዘመናት በነበሩ ነገሥታትና መሪዎች

«ኢትዮጵያ ዲፕሎማሲዋን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





## አርሶ አደሮች በ446 ሄክታር መሬት ላይ የሻይ ቅጠል ምርት እያለሙ ነው

ገጽ 6

## ለአማራ ክልል የአረንጓዴ ዐሻራ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች እየተዘጋጁ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ለ2016 ዓ.ም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች እየተዘጋጁ መሆኑን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። ከአምስት ሚሊዮን በላይ ሰዎች በችግኝ ተከላው እንደሚሳተፉ

ለአማራ ክልል የአረንጓዴ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






አቶ ብናልፍ አንዱዓለም

# ወጣቶች የሠላም አምባሳደር ሆነው ለሀገራዊ ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ እየተሠራ ነው

## - እስካሁን 50 ሺህ ወጣቶች በፕሮግራሙ ተሳትፈዋል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች የሠላም አምባሳደር ሆነው በሀገር ግንባታው ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ እየተሠራ መሆኑን የሠላም ሚኒስቴር አስታወቀ። እስካሁን 50 ሺህ ወጣቶች በፕሮግራሙ መሳተፋቸውም ተገልጿል።

የሠላም ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዱዓለም እንደገለጹት፤ ወጣቶች የሠላም አምባሳደር ሆነው በሀገር ግንባታው ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ሥልጠና ይሰጣቸዋል።

ያለ ወጣቶች ንቁ ተሳትፎ የሀገሪቱን መጻዒ ዕድል የተሻለ ማድረግ አይቻልም ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ፕሮጀክቱ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ሥልጠና በመውሰድ በሀገራዊ ግንባታ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ፕሮጀክቱ ከሁሉም ክልሎች የተውጣጣና ከፍተኛ ትምህርትን ያጠናቀቁ ወጣቶች እንደሚሳተፉበት ጠቅሰው በተዘጋጀው ካሪኩለም መሠረት በተለያዩ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለአንድ ወር ያህል እንደሚሠለጥኑ ገልጸዋል።

ሥልጠናውን የወሰዱ ወጣቶች ለስድስት ወራት ከክልላቸው ውጪ በሚገኙ ክልሎች ቆይታ ያደርጋሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሠላም አምባሳደር በመሆን በሄዱበት ክልል ሕዝብ ጋር እንዲሠሩ ይደረጋል ብለዋል።

የሠላም ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን ለሀገራዊ ዓላማ እያሠለጠነ እንደሚገኝ በመግለጽ ወጣቶች የሀገሪቱን መልካም እሴቶችን አውቀው ለሠላም ግንባታ የድርሻቸውን እንዲወጡ የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል።

ተቋሙ ይህን ተግባር መሥራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን 50 ሺህ ወጣቶች በፕሮግራሙ መሳተፋቸውን ጠቅሰው ፕሮግራሙ ከፍተኛ ሀገራዊ ተልዕኮ ያለው በመሆኑ በስፋት የሚሠራበት መሆኑን ገልጸዋል።

ወጣቶች የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውንም ባሉበት ክልል ሲማሩ እንደሚስተዋል ጠቅሰው ይህም ከክልላቸው ውጪ ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል እንዲያውቁ ማድረጉን ገልጸዋል።

ፕሮግራሙ ወጣቶች የሕዝቦችን ባሕል፣ ቋንቋ፣ ሥነ ልቦና እንዲያውቁ ዕድል ይፈጥራል ያሉት ሚኒስትሩ፣ በተለይም የወጣቶች አመለካከት፣ ክህሎትና ሞራልን በመገንባት፣ አንዱ ሌላውን ባሕልና እሴት እንዲገነዘብ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

ሀገር የሚገነባው ሁሉም የራሱን አጥር በመገንባት ሳይሆን አብሮነትን እያጠናከሩ በመሄድ መሆኑን በመግለጽ ፕሮግራሙ ሀገራዊ አንድነትንና ማኅበራዊ ትስስርን ለማጠናከር ትልቅ አስተዋፅዖ እያደረገ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም የሠላም አምባሳደር የሆኑ ወጣቶችን አሠልጥኖ በየክልሉ የማሠማራቱ ሥራም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

# የውጭ ጉዳይ ሠራተኞችና አምባሳደሮች ለመቄዶንያ ድጋፍ አደረጉ

አማን ረሺድ



አዲስ አበባ፡- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሠራተኞችና በተለያዩ ሀገራት ተመድበው የሚያገለግሉ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች የጥምቀት በዓልን ምክንያት በማድረግ ለመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን ማዕከል ከ750 ሺ. ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ አደረጉ። ከገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪም በማዕከሉ ለሚገኙ አረጋውያን ማዕድ አጋርተዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን፤ የሚኒስቴሩ ሠራተኞችና አምባሳደሮች ለመቄዶንያ የሚያስፈልገውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በዘላቂነት ይቀጥላል ብለዋል።

ከተለያዩ ሀገራት የተሰባሰቡ አምባሳደሮች በሚገኙባቸው ሀገራት ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር ለማዕከሉ ሀብት የማሰባሰብ ሥራ እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጉዳዮች ጄኔራል ዳይሬክተር አቶ አብዱ ያሲን በበኩላቸው፤ መቄዶንያ የሰብዓዊነት ጥግ ማሳያ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ ሚኒስቴሩ ማኅበረሰብ አቀፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሚሲዮኖችን በማስተባበር ድጋፍ እንደሚያደርግ አመላክተዋል።

በፈረንሳይ የኢፌዴሪ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ማሕሌት ኃይሉ በበኩላቸው፤ ወደ ማዕከሉ ሲመጡ የመጀመሪያቸው መሆኑን ገልጸው፤ ከሥራቸው ጎን ለጎን በማዕከሉ የሚገኙ አረጋውያንን በማንኛውም መንገድ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

የመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ቢንያም በለጠ በበኩላቸው፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እስካሁን ላደረገው ድጋፍ አመስግነው፤ አሁን ላይ የአረጋውያን ቁጥር እየጨመረ በመሆኑ የሚኒስቴሩ ድጋፍ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

አምባሳደሮች ባሉበት ሀገራት ያሉ ዲያስፖራዎችን በማነጋገር ለማዕከሉ የሚያደርጉትን ድጋፍ እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቅርበዋል።

በማዕከሉ ሰባት ሺህ 500 በላይ አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን አገልግሎት እያገኙ መሆኑን ገልጸው ወደ ማዕከሉ በመምጣት፣ በ8161 አጭር የጽሑፍ መልዕክት በመላክ እንዲሁም በጎ-ፈንድሚ ሁሉም ዜጋ ድጋፍና እገዛ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

በተለያዩ ሀገራት የተመደቡ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች የጥምቀት በዓልን ምክንያት በማድረገ መቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን ማዕከልን ጎብኝተዋል።

# በመዲናዋ በሌማት ትሩፋት 4 ሚሊዮን ሊትር የሚጠጋ የወተትና 42 ሚሊዮን የእንቁላል ምርት ተገኝቷል

ቃልኪዳን አሳዬ





አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት ከሦስት ሚሊዮን 820 ሺህ በላይ ሊትር ወተት፣ 12 ሺህ 342 ቶን ሥጋ፣ ከአስር ሺህ ኪሎ ግራም በላይ ማርና ከ42 ሚሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት መገኘቱን የአዲስ አበባ ከተማ የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ፋሩቅ ጀማል ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን የኑሮ ውድነት በመቀነስ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል።

በተያዘው በጀት ዓመት ተግባራዊ መደረግ በጀመረው በሁለተኛ ዙር የሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ ከሦስት ሚሊዮን 820ሺህ በላይ ሊትር ወተት፣ 12 ሺህ 342 ቶን የዶሮና የተለያዩ እንስሳት ሥጋ፣ 331 ኪሎ ግራም የዓሣ ምርት፣ ከአስር ሺህ ኪሎ ግራም በላይ ማርና ከ42 ሚሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት መገኘቱን አቶ ፋሩቅ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ፋሩቅ ገለጻ፤ በዘርፉ የተሰማሩ ነባር ተሳታፊዎችን ከማስቀጠል አንጻር በተከናወኑ ተግባራት በዕፅዋት ዘርፍ 247ሺህ 557 እንዲሁም በእንስሳት ዘርፍ 68ሺህ 268 በድምሩ 315ሺህ 825 ዜጎች እየተሳተፉ ሲሆን በተቋም ደረጃ ከ1ሺህ ስድስት መቶ በላይ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፣ የአስተዳደር ተቋማት እና የሌሎችንም ተሳትፎ ማስቀጠል ተችሏል።

መርሐ-ግብሩን ስኬታማ ለማድረግ በዕፅዋትና በእንስሳት ዘርፍ ከ56 ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በመለየትና ሥልጠና በመስጠት ወደ ዘርፉ ማስገባት የተቻለ ሲሆን፤ እንዲሁም በርካታ አዳዲስ የመንግሥትና የግል ተቋማትን ተሳትፎ ማሳደግ መቻሉን አቶ ፋሩቅ አስታውቀዋል።

የወተት ላም ዝርያ ማሻሻል በሌማት ትሩፋት ፕሮግራም በተለየ ትኩረት ከሚሠሩ ተግባራት መካከል አንዱ መሆኑን ያነሱት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን እና መኖ የማቅረብ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ከመርሐ-ግብሩ ጋር ተያይዞ በእንስሳት እርባታና በሌሎች የግብርና ሥራዎች ላይ ተሳትፎ ማድረግ የሚፈልጉ ዜጎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ በመዲናዋ የሚገኙ ክፍት ቦታዎች ለከተማ ግብርና እንዲውሉ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ዜና

# ዞኑ ከቱሪዝም ዘርፍ ከ5 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ብር አግኝቷል

## -78 የቱሪዝም መዳረሻዎች ተለይተው እየለሙ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

ወሊሶ፡- የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በስድስት ወራት ውስጥ ከቱሪዝም ዘርፍ ከ5 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ ማግኘቱን የዞኑ ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። በዞኑ 78 የቱሪዝም መዳረሻዎች ተለይተው እየለሙ መሆኑም ተነግሯል ።

በኦሮሚያ ክልል የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፈካንሰ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በዞኑ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ ከቱሪዝም ዘርፍ ከሀገር ውስጥና የውጪ ጎብኝዎች አምስት ሚሊዮን 595 ሺህ ብር ገቢ ተገኝቷል።


አቶ ፈካንሰ ገመቹ

በዞኑ ባለፉት ስድስት ወራት ከአራት ሺህ በላይ የሀገር ውስጥ ጎብኝዎች እና ከሁለት ሺህ 500 በላይ የውጪ ጎብኝዎች አካባቢውን ጎብኝተዋል ያሉት ኃላፊው፤ በዞኑ አንዳንድ አካባቢዎች የተለያዩ የፀጥታ ስጋቶች ባይፈጠሩ ከዚህ ቁጥር በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስት ማስተናገድ ይቻል ነበር ሲሉ ገልፀዋል።

በተለይ የሠላም አለመኖር የውጭ የቱሪስት ፍሰቱ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ አለው ያሉት ኃላፊው፤ በአሁኑ ወቅት በዞኑ ሁሉም ወረዳዎች እና አካባቢዎች ሠላም መስፈኑን አመላክተዋል። በአካባቢው ከፍተኛ የቱሪዝም ፍሰት ለማምጣት ተጨማሪ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

በዞኑ ለቱሪዝም መስሕብ የሚሆኑ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ቦታዎች ተለይተው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማስጀመር እየተሠራ መሆኑንም አያይዘው ጠቅሰዋል።

በዞኑ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በገበታ ለሀገር የተገነባው እና ለምርቃት የበቃው የወንጪ ደንዲ የቱሪዝም ስፍራ የዞኑን ቱሪዝም በከፍተኛ ሁኔታ አነቃቅቶታል ያሉት ኃላፊው፤ ዞኑ ያሉትን ፀጋዎች አሟጦ ለመጠቀም ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን አመላክተዋል።

በዞኑ የአዳዲ ማርያም፣ አዋሽ መልካ ቁንጡሬ፣ ዋሻዎችና ትክል ድንጋዮች እንዳሉ አንስተው፤ አመያ፣ ቀርሳ፣ ሰደንሰዶ እና ሌሎች ወረዳዎች የቱሪዝም መስሕቦችን ለማልማትና የመሠረተ ልማት ተደራሽነታቸውን ለመጨመር እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዞኑ 78 የቱሪዝም መዳረሻዎች ተለይተው እየለሙ መሆኑም ኃላፊው አብራርተዋል።

በዞኑ ያሉ ቅርሶችን በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አንድምታ ያለው ውጤት እንዲያመጡ ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ፈካንሰ፤ አዳዲስ የቱሪዝም ሀብቶች እንዲካለሉ፣ ያረጁት ይዘታቸውን ሳይለቁ እንዲታደሱ እና መሠረተ ልማት እንዲሟላላቸው የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ገልፀዋል።



# በኦሮሚያ 50 በመቶ የገጠር መሬት በካዳስተር ሥርዓት ተመዝግቧል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-በኦሮሚያ ክልል 50 በመቶ የገጠር መሬት በዘመናዊ የካዳስተር ሥርዓት መመዝገቡን የኦሮሚያ መሬት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ አቶ ጉታ ላቹሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የመሬት ካዳስተር ሥራ በከተሞችና ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

የመሬት ካዳስተር ሥራው ከ40 በላይ ከተሞችና 160 በላይ ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው ያሉት አቶ ጉታ፤ 50 በመቶ የገጠር መሬት በካዳስተር ተመዝግቧል ብለዋል።

ከ40 በላይ ከተሞች ላይ የተጀመረው የካዳስተር ሥራ በ23 ከተሞች ላይ በተያዘው ዓመት ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የካዳስተር ሥራው በከተሞች የሚታየውን የመሬት ወረራ፣ ሕገ ወጥ ግንባታን ለማስቀረት እገዛ እያደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ቢሮው የመሬት ሀብት ለመመዝገብና ለማወቅ የሚያስችሉ ሥራዎች እየሠሩ እንደሚገኝ የገለጹት ኃላፊው፤ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አሠራሮችን ወደ ዲጂታል የመቀየርና የመሬት ይዞታዎችንና ባለቤቶች የመለየት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በክልሉ የመሬት ምዝገባ በመንግሥት፣ የወልና፣ የግለሰቦች በሚል በመመዝገብ ላይ መሆኑን አስታውቀው፤ ከወረቀት ሥርዓት ወደ ዲጂታል ተቀይሮ በቢሮው ዳታ ሴንተር መረጃዎች እየተጠናከሩ መሆኑን አስረድተዋል።

በኦሮሚያ በተደረገ የመሬት አጠቃቀም ጥናት መሠረት 37 ሚሊዮን ሄክታር መሬት መኖሩን የገለጹት ኃላፊው፤ በጥናቱም ለግብርና፣ ለከብቶች እርባታ፣ የከርሰ ምድር ውሃ መገኛን ጨምሮ፣ ለኢኮ ቱሪዝምና ለኢንቨስትመንት የሚሆን መሬት ልየታ መደረጉን ገልጸዋል።

የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት አተገባበር ላይ ከአርሶ አደሩ ጋር ምክክር መደረጉን አመላክተው፤ አርሶ አደሩ በመሬት አጠቃቀም ሥርዓቱ ደስተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

አርሶ አደሩ መሬት ያለ አግባብ እንዳይታረስ፣ ደን እንዳይመነጠር እያደረገ መሆኑንም አስረድተው፤ ማኅበረሰቡ ለዘመናዊ የካዳስተር ሥራው ትግበራ ከፍተኛ አቅም ሆኖ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የመሬት ቢሮው ዜጎች የሚማረሩበት እንዳይሆን አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም የግለሰቦች፣ የሠራተኞችና የኢንቨስትመንት ፋይሎች ዲጂታል ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።


አቶ አድማሱ ሞርካ

# በክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት ከ73 ሺ በላይ ዜጎች የንጹሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆነዋል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተያዘው በጀት ዓመት በስድስት ወራት ውስጥ የንጹሕ መጠጥ ውሃን ተደራሽ ለማድረግ በተሠራው ሥራ 73 ሺህ 812 ለሚሆኑ የገጠርና የከተማ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የክልሉ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የውሃና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ አድማሱ ሞርካ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ለሚገኙ ዜጎች የንጹሕ መጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ እቅድ ተይዞ ወደ ሥራ ተገብቷል። በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ 73 ሺህ 812 ለሚሆኑ የገጠርና የከተማ ነዋሪዎች የንጹሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። ይህም 62 በመቶ የነበረውን የንጹሕ የመጠጥ የውሃ ሽፋኑን ወደ 67 በመቶ ከፍ እንዲል አድርጎታል።

በክልሉ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች የሚኖሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 800ሺህዎቹ የንጹሕ ውሃ ተጠቃሚ ናቸው። ቀሪውን የማኅበረሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የክልሉን ማኅበረሰብ የንጹሕ መጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ያለው ሥራ አበረታች ቢሆንም ክልሉ ካለው የተፈጥሮ ሀብት አንፃር በቂ አለመሆኑን አስረድተዋል። በክልሉ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ሙሉ ለሙሉ በመጠቀም የንጹሕ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ላልሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

« ከዚህ በፊት የነበረው ንጹሕ የመጠጥ ውሀ ተደራሽነት አነስተኛ የሚባል ነበር፤ ማኅበረሰቡም ስለ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ጠቀሜታ ግንዛቤው አልነበረውም፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ ብዙ ሥራ ቢሮው ሠርቷል። በዚህም 800 ሺህ ዜጎችን የንጹሕ የመጠጥ ውሃ ተደራሽና ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። ማኅበረሰቡም ስለ ንጹሕ መጠጥ ውሃ ጠቀሜታ ያለው ግንዛቤ በማደጉ የንጹሕ የመጠጥ ውሃ የመጠቀም ፍላጎቱ ጨምሯል፤ የማኅበረሰቡን ፍላጎት ለማሟላትና ጥያቄውን ለመመለስ በትኩረት እየተሠራ ነው» ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ አቶ አድማሱ ማብራሪያ፤ በ2015 በጀት ዓመት የንጹሕ የመጠጥ ውሃ ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በተሠራው ሥራ 62 በመቶ የሚሆነው የማኅበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በቀጣይ የክልሉን ማኅበረሰብ የንጹሕ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ አራት ትላልቅ የውሃ ፕሮጀክቶች እየተሠሩ ናቸው።

እየተገነቡ ካሉት አራት የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ውስጥ ሁለቱ ግንባታቸው ተጠናቆ ለምረቃ ዝግጁ ሆነዋል ያሉት አቶ አድማሱ፤ አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩም በክልሉ ያለውን የውሃ ሽፋን ከ15 እስከ 20 በመቶ እንደሚያሳድገው ይጠበቃል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመንግሥት ጥረት የመጪውን ትውልድ ዕጣ ፈንታ ቀያሪ ነው!

ኢትዮጵያውያን የረጅም ሀገረመንግስት ባለቤት የሆኑበት ሆነ ሀገረ መንግስቱን አጥንተው ማቆየት የቻሉበት ትልቁ ሚስጥር ብሄራዊ ጥቅሞቻቸው በየትኛውም ሁኔታ አሳልፎ ያለመስጠት ማኅበራዊ ማንነት ባለቤት መሆናቸው ነው። ይህ በብዙ ጥንቃቄ እና እንክብካቤ /አስተምሮ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ማንነት የዚህ ትውልድም መገለጫ ነው።

የቀደሙት ትውልዶች በየዘመኑ የተከሰቱ ሀገረ መንግስቱን ሆነ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንን የሚፈታተኑ የውስጥና የውጪ ፈተናዎች፤ የሀገርና የሕዝብን ጥቅም ባስቀደመ መንገድ ከፍ ባለ መስዋዕትነት መሻገር ችለዋል፤ በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያተረፈ ማንነት ፈጥረው አልፈዋል።

ይህ የፈጠሩት ማንነት ቀጣዩ ትውልድ አንገታቸውን አቅንተው እንዲሄዱ አስችሏል፤ በብዙ የማንነት ቀንበር ጎብጠው ዘመናት ላስቆጠሩ ሕዝቦች መንፈሳዊ መነቃት በመፍጠር ቀና ብለው የሚሄዱበትን፤ ዕጣፈንታቸውን በራሳቸው የሚወስኑበትን እድል በመስዋዕትነታቸው ህያው ማድረግ እንዲችሉ ረድቷቸዋል።

ይህ ትናንቶቻችንን ያደመቀው፤ ለዛሬያችን አቅም የሆነንና ነገዎቻችንን በብዙ ተስፋ እንድንጠብቅ ያደረገን ጥቅሞቻችን ላይ ያለመደራደር ብሔራዊ ማንነታችን፤ የዚህ ትውልድ መገለጫ ሆኖ ስለመቀጠሉ በዓባይ ግድብ ግንባታ ላይ በተጨባጭ የታየ " ይቻላል "በሚል አዲስ ትርክት ትውልዱን ያንቀሳቀሰ ነው።

ይህ ትርክት ትውልዱ ሀገሪቱ አስተማማኝ እና ፈጣን የወደብ አገልግሎት የምታገኝበትን አዲስ ተጨማሪ የታሪክ ምዕራፍ እንዲጽፍ አቅም ፈጥሯል። የዝምታን መጋረጃ ገፍፎ፤ ከራሱ አልፎ የትውልዶችን ዕጣ ፈንታ ሊቀይር በሚችል ብሩህ ተስፋ መንቀሳቀስ እንዲችል ረድቶታል።

በቀደሙት ዘመናት ሀገራችን እንደ ሀገር ከአንድም በላይ የባህር ወደብ ባለቤት እንደነበረች የታሪክ ሰነዶች ያረጋገጡት፤ ወደፊትም ሊያረጋግጡት የሚችሉት እውነታ ነው። በነዚህ ዘመናት ለነበሩ መንግስታት ግዝፈትም እነዚህ ወደቦች በአንድም ይሁን በሌላ የነበራቸው አስተዋጽኦ ከፍያለ እንደነበር ይገመታል።

ለሀገረ መንግስቱ ጥንካሬ የወደቦቹ ግልጋሎት የቱን ያህል ከፍያ እንደሆነ፤ ከሁሉም በላይ እንደ ሀገር ወደብ አልባ በሆንባቸው ስስት አስርት ዓመታት ያጋጠሙን ችግሮች፤ ችግሮቹን ለመሻገር እየከፈልነው ያለው ዋጋም ሆነ፤ ችግሮቹ ተስፋ ባደረግናቸው ነገዎቻችን ላይ ያጠሉትን ጥላ በአግባቡ መመልከት ተገቢ ነው።

ሀገሪቱ ያለችበት የቀይ ባህር አካባቢ ካለው ጂኦ- ፖለቲካዊ ጠቀሜታ አንጻር የብዙዎችን ቀልብ የሳበ ነው፤ ከዚያም በላይ አሁነኛው የዓለም ፖለቲካ ተገማችነት አስተማማኝ አይደለም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ 120 ሚሊዮን ሕዝብ ይዞ በየትኛውም መልኩ መዘናጋት በሀገር ላይ የከፋ ጥፋት የመጋበዝ ያህል ነው።

በተለይም ዓለም በብዙ ፍላጎቶች ውጥረት ውስጥ በምትገኝበትና ውጥረቶቹ እያስከፈሉ ያለው የከፋ ዋጋ በተጨባጭ እየታየ ባለበት፤ ወዳጅነትና ጠላትነት በግልጽ መስመር ተለይተው በማይታዩበት፤ ብሔራዊ ጥቅም የጥቅሞች ሁሉ "አልፋና ኦሜጋ " በሆነበት ዓለም ራስን በአግባቡ ማዘጋጀት ለነገ የሚባል የቤት ስራ አይደለም።

ከዚህ አንጻር መንግስት ካለበት ኃላፊነት አኳያ ዝምታዎችን እየሰበረ፣ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንን ለማስጠበቅ፤ ከዚያም አልፎ ሀገርን እንደሀገር የህልውና ስጋት ውስጥ የሚከቱ አደጋዎችን ከወዲሁ ለመከላከል የሚያደርገው ስትራቴጂያዊ ጥረት የዜጎችን እውቅና እና ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚፈልግ ነው።

በተለይም አሁን ላይ ሀገሪቱን አስተማማኝ የወደብ ባለቤት በማድረግ፤ ከወደብ አገልግሎትም ሆነ፤ የወደብ ባለቤት በመሆን የሚገኝ ስትራቴጂክ ተጠቃሚነትን ተጨባጭ ለማድረግ የሚያደርገው በብዙ ፈተናዎች የታጀበ ጥረት ፍሬ እንዲያፈራ መላው ሕዝባችን ዓባይን ለመገደብ ያደረገውን ርብርብ ያህል በተጠናከረ መንገድ ሊደግመው ይገባል።

ይህ የመንግስት ጥረት፣ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ አዲስ ብሔራዊ ጥቅምን የማስከበር ትርክት መጻፍ የሚያስችል መልካም ዕድል ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ትውልዱ በ"ይቻላል" መንፈስ ለጀመረው የበለጸገች ሀገር ግንባታ ስኬት ትልቅ አቅም፣ ተጨባጭ ተሞክሮ ተደርጎ የሚወሰድ፤ የመጪዎቹን ትውልዶች ዕጣ ፈንታ ቀያሪ ነው !


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ትኩረት የዲጂታል ኢትዮጵያን ጉዞ ለሚያፋጥኑ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት

**ዘካርያስ**

በዓለም ላይ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በሚያስገርም ፍጥነት እየተጓዘ ይገኛል፤ ቴክኖሎጂው ዓለምን ያንድ መንደር ያህል ማድረግ ከጀመረ ቆይቷል፡፡ የመረጃ ለውውጡ፣ ክፍያው፣ ትምህርቱ፣ ሕክምናው፣ ወታደራዊው እንቅስቃሴ፣ ወዘተ በእዚህ ቴክኖሎጂ እየተሳለጠ መሆኑም ይህንኑ ያመለክታል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሰው ሰራሽ አስተውሎት/አርተፊሻል ኢንተለጀንስ/ የሰው ልጅን ስራዎች እየተካ ስራዎች ይበልጥ የሚፋጠኑበትን ሁኔታ እየፈጠረ ነው። ያደጉት ሀገሮች ይህን ቴክኖሎጂ ብዙ ርቀት በመጓዝ የልማታቸው፣ የደህንነታቸው፣ ወዘተ ተጨማሪ አቅም አርገውታል፡፡

የሀገራችን መንግስትም የዲጂታል ዘርፉን መሰረታዊነት ከግምት ውስጥ በማካተት ለእዚህ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ትኩረት ሰጥቷል። ይህም ተከትሎም ቴክኖሎጂው እየተስፋፋ የልማት፣ የጸጥታው ዘርፍ ተጨማሪ አቅም እየሆነ መጥቷል፡፡ መንግስት የቴክኖሎጂው አገልግሎት ከዚህም በላይ እንዲሰፋ ይፈልጋል፡፡ ለእዚህም ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ለተግባራዊነቱ መስራቱን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ዘርፉን በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመት መሪ እቅድ ከአምስቱ የምጣኔ ሀብቱ ምሰሶዎች አንዱ አድርጎታል፡፡ ተቋሙ ፊትም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርነት፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተዋቅሮ ራሱን ችሎ እየሰራ ነው። ቴክኖሎጂው ሊስፋፋባቸው የሚችሉ አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላይም ይገኛል፡፡

አንድ ለእናቱ ከነበረው የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪው ኢትዮ ቴሌኮም በተጨማሪ ሳፋሪ ኮም የሀገሪቱን የቴሌኮም አገልግሎት ስራ መቋደስ መጀመሩ እንዲሁም ተመሳሳይ ኩባንያዎች ዘርፉን መቀላቀል እንዲችሉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረው እየሰራባቸው መሆናቸውም ይህንኑ ያመለክታል፡፡

ቀደም ሲል ዓለም አቀፍ ተቋማትና ያደጉት ሀገሮች መንግስት እንደ ኢትዮ ቴሌኮም ያሉትን ተቋማት ወደ ግሉ ዘርፍ እንዲያዘዋውር፣ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ዘርፎች በሀገሪቱ የሚሰሩበትን ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥር ሲወተውቱ ኢትዮ ቴሌኮምን መሸጥ ማለት የምትታልብ ላምን እንደመሸጥ ይቆጠራል የሚል ምላሽ ይሰጥ ነበር፡፡

በአሁኑ ወቅት ግን ዘርፉን ለሚያሻሽሉ ማናቸውም ኢንቨስትመንቶች መንግስት በሩን ወለል አርጎ ከፍቷል። የዚህን ተቋም የተወሰነ እጅ ለግሉ ዘርፍ ለማዞርም ቁርጠኛ መሆኑ ይታወቃል። ይህ ሁሉ የሆነው የቴሌኮም ዘርፉን ለማዘመን፣ ዘርፉ በቀጣይ መስጠት ያለበትን አገልግሎት እንዲሰጥ በማሰብ ነው።

እንደሚታወቀው፤ ዲጂታል ኢትዮጵያን በ2025 እውን ለማድረግ ስትራቴጂ ተነድፎ ወደ ትግበራ ከተገባ ዓመታት ተቆጥረዋል። የቴሌኮም አገልግሎቶች ቀደም ሲል ከነበሩበት አቅም አኳያ በአይነትም በጥራትም በተደራሽነትም እየተስፋፉ የመጡበት እንዲሁም በቴክኖሎጂዎቹ አማካይነት ዲጂታል አገልግሎት እየተስፋፋ የመጣበትን ሁኔታም ከዚሁ አኳያ መመልከት ይቻላል፡፡

ደመወዝ በዲጂታል የክፍያ አማራጮች አማካይነት በባንክ በኩል መፈጸም ከጀመረ ቆይቷል፤ እንደ ውሃ ኤሌክትሪክ፣ ቴሌኮምና የመሳሰሉት የአገልግሎት ክፍያዎችን ለመፈጸም ተቋማቱ ዘንድ በግንባር መገኘት ቀርቷል፤ ለአገልግሎት የሚደረጉ ምዝገባዎችን፣ ግብርን፣ የነዳጅ ክፍያን ፣ ወዘተ. በእዚህ ቴክኖሎጂ መክፈል ውስጥ ተገብቷል ፡፡ የመንግስት ግዥዎች በእዚሁ አገልግሎት መፈጸም ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ከባንክ ባንክ፣ በአንድ ባንክ ውስጥ ከአንድ አካውንት ወደሌላ አካውንት ገንዘብ ለማዘዋወር ባንክ ቤት መሄድ አያስፈልግም፡፡

ሀገሪቱ ይህን የአገልግሎት አሰጣጥ ከጀመረች ብዙ ዓመታትን ባታስቆጥርም፣ በቴክኖሎጂው በኩል በትሪሊዮን ብሮች መንቀሳቀስ ጀምረዋል። የፋይናንስ ተቋማትና የቴሌ ብር ሪፖርቶችን ዋቢ ያደረጉ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎችም ይህንኑ ያመለክታሉ፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን ዋቢ ያደረገውና በታህሳስ ወር የመጀመሪያ ሳምንት/ታህሳስ 7/ የወጣ የአዲስ ዘመን እትም እንዳመለከተው፤ በስድስት ወራት በኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ዝውውር ከአንድ ትሪሊየን ብር በላይ ተዘዋውሯል፡፡ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ/ር እዮብ ተካልኝ የዲጂታል ከጥቂት ወራት በፊት እንደገለጹትም፤ የክፍያ አማራጮቹ የጥሬ ገንዘብ ዝውውሩን ቀንሰውታል፤ በዲጂታል አማራጮች በዓመት እስከ አራት ትሪሊዮን ብር ድረስ እየተዘዋወረ ነው፡፡

ይህ መሆኑ ሀገሪቱ ጥሬ ገንዘብ ለማተም የምታወጣውን ወጪ ያስቀራል፤ በጥሬ ገንዘብ ዝውውር ወቅት ሊደርስ የሚችል ጥቃትንም ያስቀራል፤ በጥሬ ገንዘብ እጥረት ሳቢያ ከባንኮች ገንዘብ ለማውጣት በሚፈለግበት ወቅት ሊያጋጥም የሚችለውን የጥሬ ገንዘብ እጥረትም ያስቀራል፡፡ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርንም ያስቀራል፡፡

በዘርፉ እየተመረቁ የሚወጡ ኢትዮጵያውያን ብዛት የትየለሌ ሆኗል፤ እነዚህ ዜጎች ሶፍትዌሮችን በማልማት፣ የቴክኖሎጂውን ቁሳቀስ በመገጣጠምና በመጠገን፣ የኔት ወርክ መሰረተ ልማት በመዘርጋት ወዘተ ዘርፎች ተሰማርተዋል። ከዚህም አለፍ ብለው በሀገር ቤት ሆነው ለውጭ ኩባንያዎች ሶፍትዌር የሚያለሙበት ሁኔታም እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉሉ፡

ስፋትና ጥልቀቱ ይለያይ እንጂ በአሁኑ ወቅት ዘርፉ የማያስፈልግበት የስራ ዘርፍና ተቋም የለም። እነዚህን አገልግሎቶች ለመስጠት በርካታ ሶፍትዌሮች እንዲለሙ እየተደረገ ነው። በርካታ ስራዎች ቢሮ መግባት ሳይስፈልግ ከመኖሪያ ቤት በመሆን የሚሰሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፤ በኮቪድ ወቅት የዚህ ቴክኖሎጂ ፋይዳ በሚገባ ተለይቷል። ስራን ከቤት ሆኖ መስራት አስችሏልና፡፡ በሽታው

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# አርሶ አደሮች በ446 ሄክታር መሬት ላይ የሻይ ቅጠል ምርት እያለሙ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮች በ446 ሄክታር መሬት ላይ የሻይ ቅጠል ምርት እያለሙ መሆኑን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን ገለጸ። እስካሁን ሦስት ሺህ 100 ቶን ቡና ለማዕከላዊ ገበያ ቀርቧል።

በክልሉ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አሥራት መኩሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳመለከቱት፤ በክልሉ የሚገኙ 502 አርሶ አደሮች በ446 ሄክታር መሬት ላይ ለፋብሪካዎች የሚቀርብ የሻይ ቅጠል እያለሙ ይገኛል።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በካፋና ሻካ ዞኖች በስፋት የሻይ ቅጠል ምርት እንደሚመረት የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኢስት አፍሪካ ኩባንያ በሸካ ዞን የሻይ ምርት እያለማ ሲሆን፤ ኢትዮ አግሪ ሴፍት ደግሞ በካፋ ዞን በውሸውሸ የሻይ ቅጠል ልማት እየለማ መሆኑን ገልጸዋል።

በሁለቱ ዞኖች አካባቢ የሚገኙ አርሶአደሮች ተደራጅተው ለድርጅቶቹ የሻይ ቅጠል ምርት እያቀረቡ መሆኑን ጠቁመው፤ በኮንትራት ውል መሠረት ተደራጅተው የሻይ ቅጠል ምርት እያቀረቡ የሚገኙ አርሶ አደሮች ማሳቸው ላይ ያለውን ምርት የሚንከባከቡበት መንገድ ላይ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሻይ ቅጠል ምርት የገበያ አድማስን ከማሳደግ አኳያ አርሶ አደሮቹ አማራጭ ገበያን የማግኘት እድላቸው ውስን ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ አሁን ላይ አልሚ ድርጅቶቹ በሚያቀርቡላቸው ዋጋ እያቀረቡ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

በክልሉ የሻይ ምርት በርካታ የሻይ ቅጠል ዝርያ መኖሩን አመላክተው፤ አሁን ላይ በስፋት የውሸውሸ ሻይ እየተመረተ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

ክልሉ በጀት ዓመቱ ወደማዕከላዊ ገበያ ለመላክ ካቀደው ሰባት ሺህ 26 ቶን የሻይ ቅጠል ምርት ውስጥ እስካሁን ሦስት ሺህ 100 ቶን የሻይ ምርት ለማዕከላዊ ገበያ መቅረቡን አስታውቀዋል።

ክልሉ በቡና፣ ቅመማ ቅመም እና የሻይ ምርት በስፋት የሚመረትበት እንደመሆኑ፤ በክልሉ ከዞን እስከ ቀበሌ የሚገኙ አርሶ አደሮች በቅንጅት ከሠሩ ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚቻል አመላክተዋል።

# በአማራ ክልል 43 ትላልቅ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል የንጹሕ መጠጥ ውሀ አቅርቦትን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ 43 ትላልቅ የውሀ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ መሆኑን የክልሉ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ኤፍሬም ምንሽር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ 43 ትላልቅ የውሃ ፕሮጀክቶችን እየገነባ ነው። በአሁኑ ወቅትም የፕሮጀክቶቹ የአፈፃፀም ደረጃ 65 በመቶ ደርሷል። በለጋሽ ድርጅቶችና በመንግሥት በጀት እየተገነቡ የሚገኙት እነዚህ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ አሁን ያለው የክልሉ 73 በመቶ የውሃ ሽፋን ተደራሽነት ወደ 76 በመቶ ከፍ ይላል።

በገጠር ለሚኖረው ማኅበረሰብ ንጹሕ መጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ አነስተኛ የውሃ ጉድጓዶች እየተቆፈሩ መሆናቸውን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ ለከተማው ማኅበረሰብ ደግሞ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ ትላልቅ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ መሆናቸውን አመልክተዋል።

ከውጪ ከሚመጡ ግብዓቶች ጋር የተያያዘና የፀጥታ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር እየተሠሩ ካሉት 43 ፕሮጀክቶች ውስጥ 35 የሚሆኑት በያዝነው ዓመት ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምሩ ተናግረዋል።

‹‹በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ተበታትነው የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ



**አቶ ኤፍሬም ምንሽር**

ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ባለውም ሥራ አንድ ሺህ 200 የሚሆኑ አነስተኛ የውሃ ጉድጓድ ለመገንባት ጥረት እየተደረገ ነው›› ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ አቶ ኤፍሬም ማብራሪያ፤ በክልሉ እየተገነቡ ከሚገኙት የውሃ ፕሮጀክቶች የጥራት ችግር ኖሯቸው በማኅበረሰቡ ላይ የጤና ችግር እንዳያደርሱ የውሃ መገኛ ቦታዎች ላይ ጥናት ይካሄዳል። የተገኘው ውሃ ለመጠጥ የሚውል መሆኑ አለመሆኑ የልየታ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ፕሮጀክቶች ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

በክልሉ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ባለ ሥራ በርካታ ጉድጓዶች ተቆፍረው የጥራት ጉድለትና ከፍተኛ የሆነ የኬሚካል መጠን በውስጣቸው መገኘቱን በመጥቀስ፤ ማኅበረሰቡም እንዳይጠቀማቸው የማድረግ ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል።

# “ኢትዮጵያ በተገቢው ዲፕሎማሲና በሰጥቶ..

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ቢያንስ የእራሳችን የምንለው ገመናችንን የምንጠብቅበትና ትብብራችንን የምናጠናክርበት የባሕር በር ያስፈልገናል ያሉት አምባሳደሩ፤ በዚህ አግባብ በተገቢው ዲፕሎማሲና በሰጥቶ መቀበል መርሕ የባሕር በር የማግኘት መብት አለን ብለዋል።

በተገቢው ጥንቃቄና ብቃት ባለው ዲፕሎማሲ እየተመራ ጉዳዩ መፍትሔ እንዲያገኝና እፎይ የምንልበት ወደብ ያስፈልገዋል ሲሉ ጠቁመዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ትልቅ ሕዝብ ይዞ የባሕር በር የሌለው ሀገር በዓለም እንደሌለ ያስታወሱት ኢንጂነር ስለሺ፤ በቀጣይ ስድስት ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ 150 ሚሊዮን ይደርሳል የሚል ትንበያ መኖሩን አመላክተዋል።

የሕዝብ ቁጥሩ ከዓለም ዘጠነኛ ያደርገናል ያሉት አምባሳደሩ፤ ለዚህ ሰፊ ሕዝብና እያደገ የሚመጣውን ኢኮኖሚ በአግባቡ ለማስተናገድ ወደብ ወሳኝ ጉዳይ ነው ብለዋል።

ከእኛ የባሕር በር ፍላጎት አኳያ በተጻጻሪው የሚቆሙ ሀገሮች ኢትዮጵያ ወደብ በማግኘቷ ተጎድተው ሳይሆን የኢትዮጵያን ማደግ በበጎ ስለማይመለከቱት የሚመጣ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አምባሳደር ኢንጂነር ስለሺ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ አቅሟን እያጠናከረችና ተፅዕኖ ፈጣሪነቷን እያጎለበተች ከመጣች ስጋት ስለሚሰማቸው ባለችበት እንድትቆም የሚፈልጉ ኃይሎች እንዳሉ ግልጽ ነው።

ኢትዮጵያን የሚጻረሩ ሀገራት ይታወቃሉ፤ እነሱ ላይ ትኩረት ሰጥተን መሥራት አለብን። የተጻራሪዎቻችንን ልክ በሚመጥን መልኩ ምላሽ በመስጠትና በመመከት የኢትዮጵያን የባሕር በር ፍላጎት በአግባቡ ማሳካት ያስፈልጋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር ያደረገችውን የባሕር በር ስምምነት ተከትሎ ጉዳዩን ከሶማሊያ ጋር ውጥረት ውስጥ ለመክተት የሚፈልጉ ኃይሎች መኖራቸውን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ በሰጥቶ መቀበል መርሕ እየተጓዘች የባሕር በር ተከልክላ ሠላማዊ የሆነ ቀጣና ሊኖር እንደማይችል የተናገሩት አምባሳደሩ፤ በጋራ ትብብር ላይ የተመሠረተ ልማትና ዕድገት ለቀጣናው ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣናን ለማሳደግ እንዴት አድርገን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትብብር መፍጠር ይገባል የሚለው ላይ ማተኮር እንጂ የኢትዮጵያን ፍላጎት ብቻ መቃወም ተገቢ አይደለም ሲሉም ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ ፖለቲካን በሕዝቦች መካከል በሚደረግ የጋራ መግባባት፣ በመሪዎች የትብብር መንፈስና በጋራ ጥቅም ላይ በተመሠረተ አግባብ ማልማት እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

አምባሳደር ስለሺ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ፍላጎትና ተጠቃሚነት በአብሮ የመሥራት መንፈስ ላይ የተመረኮዘና ለጋራ ዕድገት የሚበጅ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

# «ኢትዮጵያ ዲፕሎማሲዋን ከወገንተኝነት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም በማስከበር ላይ ያተኮረ የዲፕሎማሲ መርሕ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል ብለዋል።

በባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ በዓለም አቀፍ ሁኔታዎች በሚነሱ ግጭቶች ወይም በሁለት አካላት መካከል በሚነሱ ጦርነቶች ላይ ኢትዮጵያ አንድን ወገን መርጣ ከመደገፍ ይልቅ መካከለኛውን ቦታ ይዛ ሁኔታውን ማጤን ላይ እንደምታዘነብል የታሪክ ማስረጃዎች መኖራቸውን አስረድተዋል።

በዘጉዌ ስርወ-መንግሥት ዘመን በተነሳው የመስቀል ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥታትን ደግፋ እንድትቆም ብትጠየቅም ገለልተኛነትን በመምረጥ ጦርነቱ ላይ ያሳየችው አቋም ከማንም ያልወገነና ብሔራዊ ጥቅምን ማስከበርን አጀንዳ ያደረገ የረጅም ዘመናት የዲፕሎማሲ አካሄድ እንዳላት አንድ ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ፖለቲካ ቡድኖች አባል ብትሆንም በአንድ የኢኮኖሚ ቡድን ብቻ ተወስና ከሌሎች ጋር ያላትን ዲፕሎማሲ አታቋርጥም ያሉት ዶክተር አንተነህ፤ ለአብነት ኢትዮጵያ ወደብሪክስ ቡድን ከገባች በኋላ ከምዕራቡ ዓለም ጋር በዲፕሎማሲው መንገድ ትገነጠላለች የሚል እሳቤ ሳይሆን ሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅሟን በማስቀደም ከሁሉም ወገኖች ጋር እየሠራች ትቀጥላለች ብለዋል።

ይህ የባለብዙ ወገን ገለልተኛ አቋም ያለው ዲፕሎማሲ ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ እንደሚያመዝን ጠቁመው፤ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባጋጠሙን ፈተናዎች ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴያችን ውጤታማ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ላይ በሰሜኑ ጦርነት ወቅት፣ በአካባቢው አለመረጋጋትና በዓባይ ግድብ ውይይት ላይ አስጨናቂ የዲፕሎማሲ ጫናዎች ከተለያዩ አካላት ሲደርስ እንደነበር አስታውሰው፤ ከጫናዎቹ አንጻር በባለብዙ ወገን ብሔራዊ ጥቅምን የማስከበር ሥራ ውጤታማ ከነውን መደረጉን ማየት እንደሚቻል አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ በዘመናት ቅብብሎሽ ዲፕሎማሲዋን ከወገንተኝነት በራቀ መልኩ ያከናወነችበትን መንገድ የቀጣዩ ዘመን ዲፕሎማቶች በሰፊው ሊማሩበት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

# ለአማራ ክልል የአረንጓዴ አሻራ አንድ ነጥብ ሰባት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተገልጿል።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አልማዝ ጊዜው(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

በ201 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የደን፣ የፍራፍሬና ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያላቸው ችግኞች እንደሚተከሉ ገልጸው፤ ችግኞች በ84 ሺህ ጣቢያዎች ላይ እየተዘጋጁ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በ2016 ዓ.ም በሚካሄደው የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር በርካታ ችግኞችን ለመትከል መታቀዱን ጠቅሰው፤ በክልሉ የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ መርሐ-ግብር አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሰዎች እንደሚሳተፉ ገልጸዋል።

የአፈርና ጥበቃ ሥራ በተሠሩባቸው አካባቢዎች የአትክልትና የፍራፍሬ ችግኞች እንደሚተከሉ ገልጸው፤ 20 በመቶዎቹ ሀገር በቀል እንደሚሆኑ አስታውቀዋል።



በቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ከ70 በመቶ በላይ የተከላ ቦታዎች መለየታቸውን የገለጹት የቢሮው ምክትል ኃላፊ፤ ክልሉ ካለበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ዝግጅቱ ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ባለፈው ዓመት በክልሉ የተተከሉ አንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞችን የመንከባከብና የመጠበቅ ሥራ በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

በ2015 ዓ.ም የክረምት ወቅት ከተተከሉ ችግኞች 84 በመቶ በላይ የሚሆኑት መጽደቃቸውን አስታውቀው፤ ኅብረተሰቡ በችግኝ ተከላ ወቅት ያሳየውን ተሳትፎ በማሳደግ የችግኝ እንክብካቤውን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል።

የተተከሉ ችግኞች የፅድቀት ምጣኔያቸው በደቡብ ጎንደር ሁለት ወረዳዎች፣ በሰሜን ወሎ አምስት ወረዳዎችና፣ በዋግኽምራ አካባቢዎች አነስተኛ ነው ያሉት ዶክተር አልማዝ፤ ችግሩን ለመቅረፍ ችግኞችን ከማዘጋጀት እስከ እንክብካቤው ያለውን የተቀናጀ ሥራ በሥልጠና መልክ ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለችግኝ ተከላው የሚረዱ የቅድመ ዝግጅት፣ የግብዓት ማቅረብ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የችግኝ ፕላስቲኮችና ከ200 ሺህ ሜትር ኪዩብ በላይ ኮምፖስት እየተዘጋጀ መሆኑን ጠቁመዋል።

በክልሉ በርካታ ተራራዎች የሚገኙ በመሆኑና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ ከዓመት እስከ ዓመት የሚሠራ መሆኑን የገለጹት ዶክተር አልማዝ፤ በክልሉ የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራ የሕልውና ጉዳይ በመሆኑ አጠናክሮ ማስኬድ ያስፈልጋል ብለዋል።

በመጨረሻም ለአረንጓዴ ዐሻራ ሥራው ውጤታማነት ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ቅንጅታዊ አሰራር- ለአርብቶ አደሩ ተጠቃሚነት

**ማህሌት አብዱል**

ኢትዮጵያ ድርቅ በተደጋጋሚ ከሚያጠቃቸው የአፍሪካ ሃገራት አንዷ ናት፡፡ በተለይም ቆላማና አርብቶ አደር የሃገሪቱ አካባቢዎች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በሚከሰቱ ድርቅ፣ ጎርፍና የአንበጣ ወረርሽኝ የመሳሰሉ ችግሮች ተጋላጭ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተውም፤ ከሀገሪቱ አጠቃላይ ስፋት 62 በመቶ የሚሆነው ቆላማ አካባቢ ሲሆን፣ በዚህ አካባቢ ደግሞ ከሀገሪቱ ህዝብ 12 በመቶ የሚሆነው ኑሮውን የመሰረተውም በዚሁ አካባቢ ነው፡፡

ይህ ቆላማና በርሃማ የሃገሪቱ አካባቢ በተደጋጋሚ በአየር ንብረት ለውጥ በከፍተኛ ደረጃ ተጎጂ ሲሆን፣ በዋናነትም ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብን ተከትሎ በሚከሰት ጎርፍና ዝናብ እጥረት አርብቶ አደሩም ሆነ የህልውናው መሰረት የሆኑት እንስሳት ለከፋ ችግር የሚጋለጡበት ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡

እምቅ የተፈጥሮ ሃብትና አቅም ያለበት አካባቢ እንደሆነ የሚጠቀሰው ይህ አካባቢ በአንፃሩ ከፍተኛ በሚባል ደረጃ ለአደጋ ስጋት ተጋላጭ መሆኑም ይገለጻል፡፡ ይህም ሁኔታ ባለው ሃብት ተጠቃሚ እንዳይሆን እያደረገው መሆኑን ነው መረጃው የሚያመለክተው፡፡

የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ኤጀንሲ በእ.ኤ.አ 2020 ያወጣው መረጃ እንደሚጠቆመው፤ ኢትዮጵያን በቀንድ ሃብቷ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም መሆን የቻለችው ከዚሁ አርብቶአደር አካባቢ ከሚገኝ የእንስሳት ልማት ሃብት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት 65 ሚሊዮን የቀንድ ከብት ፣ 40 ሚሊዮን በግ ፣ 51 ሚሊዮን ፍየል፣ ስምንት ሚሊዮን ግመል፣ 49 ሚሊዮን ዶሮ እንዳላት ይገመታል፡፡ ከዚህ ውስጥ ደግሞ 90 በመቶ የሚሆነው የእንስሳት ሃብት የሚገኘው ከዚሁ አርብቶ አደርና ቆላማ አካባቢ ነው፡፡

ኢጋድ በእ.ኤ.አ ባወጣው መረጃ ደግሞ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ወደ ውጭ ከምትልከው የቀንድ ከብት ከ200 እስከ 300 ሚሊዮን የሚገመት ዶላር የምታገኘው ከዚሁ አካባቢ ነው፡፡

ከባህል ጠለል አንድ ሺ 500 ሜትር በታች ላይ የሚገኘው ይህ ቆላማ አካባቢ በዋናነት አዋሽ ፣ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ፣ ባሮ፣ ዳዋ እና ኦሞ ወንዞች ይገኙበታል። ይሁንና በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረው አርብቶ አደር በየዓመቱ በሚከሰተውና ተከታታይነት ባለው ድርቅ የአደጋ ስጋት ተጋላጭ ሆኗል፡፡ ይህንንም አደጋ ሽሽት ቀዬውን ለቆ ለመሰደድ የተገደደው ይኸው ማህበረሰብ፣ በምግብ እህል ራሱን መቻል ተስኖት የበጎአድራጊዎች እጅ የሚጠብቅ ሲሆን ይስተዋላል፡፡

ይህንን ማህበረሰብ ከተጋረጠበት የድርቅ አደጋ ለመታደግና ሃገሪቷንም በእንስሳት ሃብቷ ተጠቃሚ ለማድረግ መንግስትም ሆነ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ፕሮጀክት ቀርፀውና በጀት መድበው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየውም፤ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረውን ማህበረሰብ ህይወት ለመታደግና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ ፕሮጀክቶች በዓለም ባንክ ፣ አሜሪካ ልማት ድርጅት፣ አውሮፓ ህብረት፣ ጀርመን ተራድኦ ድርጅት፣ አፍሪካ ልማት ባንክ የመሳሳሉት ድርጅቶች ድጋፍ እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

ይህም ድጋፍ የአርብቶ አደሩን ኑሮ ለመለወጥ ከፍተኛ እገዛ እያደረገ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ይሁንና የእነዚህ የልማት አጋሮች በተናጠል የየራሳቸውን በጀት፣ የሰው ሃይልና አቅም አሰባስበው የሚሰሩት ሥራ የሚፈለገውን ውጤት በፍጥነት ማምጣት አለማስቻሉ ይገለጻል፡፡ በተለይም ባለመናበብ በተመሳሳይ ቦታ፤ ተመሳሳይ የልማት ሥራ ለመስራት የሚያደርጉት ጥረት ችግሩን ስር ነቀል በሆነ መልኩ ለመፍታት አለማስቻሉን ነው የዘርፉ ተዋናዮች የሚያስረዱት፡፡

ማህበረሰቡን በዘላቂነት ከድርቅ ተጋላጭነት ማላቀቅ ያስችል ዘንድ እነዚህ በተናጠል የሚማስኑትን የልማት አጋር ድርጅቶች ሥራ ወደ አንድ ማምጣትና የመፈፀም አቅምን ማጠናከር ዓላማው ያደረገ ፕሮጀክት ከሰሞኑ በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ይፋ ተደርጓል፡፡ በአሜሪካ የበጎ አድራጎት ድርጅት (ዩ.ኤስ ኤይድ) ድጋፍ የሚተገበረው ይህ ፕሮጀክት በዋናነት የልማት ስራዎችን የማስተባበር፤ የማቀናጀትና የግንኙነት አግባብን ለማጠናከር ያስችላል ተብሎ እምነት ተጥሎበታል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እንድሪያስ ጌታ እንደተናገሩት፤ ከዩ.ኤስ. ኤይድ ጋር በጋራ በመሆን የሚተገበረው ይኸው ፕሮጀክት በዋናነት በአራት ክልሎች የሚገኙ ቆላማ አካባቢዎች ላይ የሚሰሩ አጠቃላይ ሥራዎችን ለማቀናጀትና ለማስፈፀም የሚያስችል ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በአሜሪካ መንግስት እርዳታ በተገኘ ሶስት ሚሊዮን ዶላር የሚከናወን ሲሆን፣ የማስፈፀም አቅም ለመገንባትና የትብብር ስራን ለማያስኬድ ያግዛል፤ ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታትም በተመረጡ አካባቢዎች ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፣ በተለይም በኦሮሚያ ክልል አርብቶአደር ዞኖች፤ ሱማሌ፤ አፋር እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኦሞ ዞን ተግባራዊ የሚደረግ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ዝርዝር ሥራዎች ተለይተው ውጤታማነትን ሊያረጋግጥ በሚችል አግባብ ተመርጦ ይተገበራል፡፡

እስካሁን ድረስ ቆላማ አካባቢዎች በተለይም በአርብቶ አደር አካባቢዎች በርካታ ፕሮክቶች መንግስታዊ፣ ሀገር-በቀልና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተለያዩ የልማት አጋሮች የሚገኘውን ሃብት ተጠቅመው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ መቆየታቸውን ዶክተር እንድሪያስ ያስታውሳሉ። ‹‹እነዚህ በተለያዩ አካላት የሚከናወኑ ስራዎች በውጤታማነት ደረጃ ሲለካ ያን ያህል የህብረተሰቡን ኑሮ ሲቀይሩ አይታዩም›› ይላሉ፡፡ እንደ ድርቅ የመሳሰሉ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሲደርሱ የእለት ደራሽ እርዳታ ከመለገስ ባለፈ ችግሩን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር አለመቻላቸውን ያስረዳሉ፡፡

‹‹በፌደራል ደረጃ በእኛም ሆነ በግብርና ሚኒስቴር፤ በክልል መንግስታት እንዲሁም በበርካታ የልማት አጋሮች የቆላማ አካባቢዎችንና አርብቶ አደሮችን ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ሁሉም በተናጠል የሚንቀሳቀስበት፤ ትብብር፤ ቅንጅት የማይታይበት፤ ተጠያቂነት የሌለበት፤ ውጤታማነት በአግባቡ የማይፈተሽበት ሁኔታ ነው ያለው›› ሲሉ ያብራራሉ። በዚህም ምክንያት በተለይም ድርቅን ለመከላከል እና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት የተሰሩ የመስኖ እና መሰል ሥራዎች አመርቂ ውጤት አለማምጣታቸውን ያመለክታሉ፡፡

ተጨባጭና አርብቶ አደሩን ማዕከል ያደረገ ለውጥ ለማምጣትም እነዚህን በተለያዩ አካላት የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ በቅንጅት መስራት እንደሚያስፈልግም ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ አቅም ሊኖር እንደሚገባ ተናግረው፤ ‹‹እስከ አሁን ድረስ በፌዴራልም፤ በክልል ደረጃም የማስተባበርና ወደ አንድ ማምጣት የሚያስችል አቅም በሚፈለገው ደረጃ አልተገነባም፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ደንብም መመሪያም አልነበረም›› ሲሉም ያብራራሉ፡፡

ችግሩ የፋይናንስ ድጋፍ እጥረት ብቻ እንዳልሆነ የሚያነሱት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በዋናነት የተገኘውን ድጋፍ አጣምሮ ለወሳኝና ተፈላጊው ልማት ማዋል አለመቻሉ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ ‹‹በአሜሪካ መንግስት ድጋፍ የሚሰራው ይህ ፕሮጀክት በአጠቃላይ በቅንጅት ለመስራትም ሆነ ይህንን ለማስፈፀም የሚያስችሉ ስልጠናዎችን፤ የቴክኒክ ድጋፎችን ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት ለመዘርጋት ያግዛል››ይላሉ፡፡ በርካታ ዜጎች ችግር ላይ የሚወድቁበትና ለእለት ደራሽ እርዳታ ፍለጋ ከቀያቸው የሚፈናቀሉበትን ሁኔታ ለማስቀረት እንደሚረዳም ያመለክታሉ፡፡

‹‹የፕሮጀክቱ ዓላማ በዋናነት ችግሮችን የሚቋቋም /ሪዚሊየንት/ ማህበረሰብ መፍጠር ነው›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህ ሲባልም የማስተባበር፤ የመፈፀምና ማስፈፀም አቅም በማጠናከር ረገድ ያለውን ክፍተት ሸፍኖ ጎን ለጎን የሚሄዱ ቅንጅታዊነት የጎደላቸው በርካታ ፕሮጀክቶችን ወደአንድ ሊያመጣ የሚችል እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ በተጨማሪም ግልፅነትና ተጠያቂነት በሚላበስበት ሁኔታ ሥራዎችን ለመስራት እንደሚረዳ ይናገራሉ፡፡

**ማህበረሰቡን በዘላቂነት ከድርቅ ተጋላጭነት ማላቀቅ ያስችል ዘንድ እነዚህ በተናጠል የሚማስኑትን የልማት አጋር ድርጅቶች ሥራ ወደአንድ ማምጣትና የመፈፀም አቅምን ማጠናከር ዓላማው ያደረገ ፕሮጀክት ከሰሞኑ በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ይፋ ተደርጓል**

ዶክተር እንድሪያስ እንደሚሉት፤ ይህ ፕሮጀክት የቆላማ አካባቢ ዜጎችን ህይወት ማሻሻል የሚያስችል ማስተባበሪያ ተደርጎ ይታያል፡፡ ትግበራው ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በይፋ የተጀመረ ሲሆን፣ በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ዝርዝር እቅዶች ፤ የምክክር መድረኮች በየክልሉ ወረዳዎች ይካሄዳሉ፡፡ ይሁንና ለዚህ ሥራ በአሜሪካ መንግስት የተመደበው በጀት ውስን በመሆኑ ሁሉንም አካባቢዎች ተጠቃሚ ለማድረግ እንደየሃብቱ ግኝት ወደፊት ተጨማሪ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡

‹‹የዚህ ፕሮጀክት ተግባራዊ መደረግ የሃብት ብክነትና ድግግሞሽ እንዳይኖር፤ ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ደግሞ በተቀናጀ አኳኋን ምላሽ መስጠት በሚያስችል ሁኔታ የተናበበ ስራ እንዲሰራ ያደርጋል›› ሲሉ ያስረዳሉ። ተጨማሪ ሃብቶች የሚገኙ ከሆነ የበለጠ በማስፋት ከአራቱ ክልሎች ውጪ ያሉ አርብቶአደር አካባቢዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል መስኖና አርብቶ አደር ልማት ምክትል ቢሮ ሃላፊ አቶ ሮባ ቱርጩ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ዝናብ በተጠበቀው ጊዜ አይጥልም፤ ቢጥልም በቂ ስለማይሆን አብዛኛዎቹ አርብቶአደሮች ለድርቅ ይጋለጣሉ፡፡ ይህንን ችግር ለመከላከል የዝናብ ውሃን በማጠራቀም መካከለኛ መስኖዎች እንዲሰሩ ተደርገዋል። ለአብነት ኦሮሚያ በተደጋጋሚ ድርቅ በሚያጠቃው ቦረና አካባቢ የተሰሩ ሰፋፊ የመስኖ መሰረተ ልማቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ኩሬዎችም ውሃ እንዲይዙ ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡

‹‹ሰው ሰርቶ ራሱን እንዲችል ለማድረግም በግብርና በኩል ውሃ የማቅረብ ሥራ እየሰራ ነው›› ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በተመሳሳይ ሌሎች ማገዝ የሚፈልጉ አካላትን በማቀናጀት በመንግስት የተጀመረው ጥረት ክፍተት እንደሚሞላም ያስረዳሉ፡፡ በፌደራልምና ክልል መንግስት የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለማሻሻል የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ በተለይም በክልሉ 40 በመቶ የሚሆነው ማህበረሰብ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር መሆኑን ጠቅሰው፣ እነዚህን አካባቢዎች ማዕከል ያደረጉ የልማት ስራዎች ከፍተኛ በጀት ተመድቦላቸው እየተሰሩ እንደሆነም ነው ያስገነዘቡት፡፡

በዋናነትም ድርቅ በሚያጠቃቸው የክልሉ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ የውሃና የመኖ እጥረት መኖሩን ያመለከቱት ምክትል የቢሮ ሃላፊው፤ የልማት አጋሮችን በማስተባበር ለማህበረሰቡ ዘላቂ ውሃና አቅርቦት ማግኘት የሚያስችሉት ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ መሆናቸውን አንስተዋል፡፡ ይሁንና ከችግሩ ስፋትና ለድርቅ ተጋላጭ ከሆነው ህዝብ ቁጥር አንፃር የሚሰሩት ሥራዎች አስተማማኝ በሆነ መንገድ ችግሩን መፍታት አለማስቻላቸውን ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል ሁሉም ሥራዎች የሚሰሩት እንደየልማት አጋሩ ፍላጎትና አቅም መሆኑንም ተናግረዋል፤ በዚህ የተነሳም አመርቂ የሚባል ውጤት አለመምጣቱን እሳቸውም የሚስማሙበት ጉዳይ እንደሆነ ነው ያስረዱት፡፡

‹‹በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረው በተለይ አርብቶ አደር እንደመሆኑ ከፍተኛ የውሃና የመኖ እጥረት አለ፡፡ ይህንንም ችግር ለመፍታት በመንግስትም ሆነ በተለያዩ አካላት ድጋፍ የሚሰሩ ሥራዎች አሉ፡፡ ይሁንና ስራዎቹ ባልተቀናጀ መልኩ የሚሰሩ በመሆናቸው የአርብቶ አደሩ ህይወት በዘላቂነት ሲለወጥ አይታይም›› ይላሉ። የዚህ ፕሮጀክት ተግባራዊ መሆን የአርብቶአደርን አቅም በተሻለ ደረጃ ማጠናከር ያስችላል ብለው እንደሚያምኑም ጠቅሰው፣ እዚህም እዚያም ያለው ሃብት በተጨባጭ አርብቶአደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ ያግዛል ባይ ናቸው፡፡

ከዚህም ባሻገር የሚነደፉ መመሪያዎች፤ የሚዘረጉ የአሰራር ስርዓቶች አርብቶ አደሩን ማዕከል ባደረገ መልኩ እንዲዘጋጁ አቅም እንደሚፈጥር ያስረዳሉ። በተለያዩ አካላት የሚሰሩ ሥራዎች ወደአንድ ማዕቀፍ ሲመጡ የሰው ሃይሉን በአንድ ጉዳይ ላይ ለማብቃት እንደሚያግዝ ይናገራሉ፡፡ ‹‹ድርቅ ፈፅሞ እንዳይመጣ ማድረግ አይቻልም፡፡ ድርቅ ሲመጣ መቋቋም መቻል ግን ትልቅ አቅም ነው›› የሚሉት አቶ ሮባ፤ የፕሮጀክቱም ዋና አላማ ይህ እንደሆነ ነው ያስገነዘቡት፡፡

የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት አማካሪ አቶ አህመድ ኢስማኤልም የፕሮጀክቱ ተግባዊ መሆን ፋይዳው ብዙ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ እንደእሳቸው ገለፃ፤ በክልሉ በርካታ ወንዞችና ተፋሰሶች ቢኖሩም አካባቢው ቆላማ እንደመሆኑ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ አቀናጅቶ መሄድ ላይ ውስንነት በመኖሩ አርብቶአደሩን በሚገባ ተጠቃሚ ማድረግ አልተቻለም፡፡ የተለያዩ የልማት ድርጅቶች ከክልሉና ከፌደራል መንግስት ጋር በመተባበርና በተናጠል ፕሮጀክት ነድፈው የሚንቀሳቀሱ ቢሆንም ሥራዎቹ በመናበብ የማይሰሩ በመሆኑ ብክነት ይስተዋላል፡፡ ያለውን ውስን ሃብት በአግባቡ መርቶ ሥራ ላይ ማዋል ባለመቻሉ አርብቶአደሩ አደጋ በመጣ ቁጥር የሌሎች እጅ ጠባቂ ይሆናል፡፡

የዚህ ፕሮጀክት ተግባራዊ መሆን ይህንን ውስን ሃብት በማቀናጀትና ወጥነት ያለው የልማት ሥራ ለማከናወን ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ የሚያነሱት አቶ ኢስማኤል፣ በተለይም በክልሉ ያሉ የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን እንዲሁም የመስኖ ልማቶች በተጨባጭ የአርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ማዕከል አድርገው እንዲከናወኑ ለማድረግ ያግዛል የሚል እምነት እንዳላቸውም አስታውቀዋል፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

## በ2016 ዓ.ም ወደ ተግባር የተገባባቸው የለውጥ ስራዎች

ግርማ መንግሥቴ

ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና በትኩረት መስክ ተለይተው እንዲሰሩ ማድረግ ለትምህርት ጥራትና በአገራችን እንዲገነባ ለምንፈልገው ብዝሃ ዘርፍ ኢኮኖሚ ወሳኝ መሆናቸውን ሳይታክት ሲናገር የቆየው የትምህርት ሚኒስቴር በያዝነው ዓመት ቃሉን አክብሮ ወደ ስራ የገባ መሆኑን፤ ቃልን ወደ ተግባር በመቀየር የለውጥ (ሪፎርም) ስራውን በማስኬድ ላይ እንደ ሆነ እየተናገረ ይገኛል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሐምሌ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ከለቀቀው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፣ እንደ አገር ያጋጠመንን የትምህርት ጥራት መጓደል ለማረም በሁሉም የትምህርት እርከን የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎች ተቀርፀዋል። መቀረፅ ብቻም ሳይሆን፣ ወደ ሥራም ተገብቷል። ሪፎርሞቹ በትምህርት ዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለማረም መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች፤ በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ የተሰነዱ ናቸው፡፡ በባለፉት አምስት ዓመታት ይህንኑ ፍኖተ ካርታና የለውጥ ምክረ ሃሳቦች በመከተል በአጠቃላይና በከፍተኛ ትምህርት ዘርፎች የሪፎርሙ ስራዎች የተተገበሩና በመተግበር ላይ ናቸው፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ እነዚህን ለውጦችና የሪፎርም ሃሳቦች በመከተል እየተተገበሩ ካሉ ጉዳዮች መካከል፤ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አመራር ብቃትን መሰረት ባደረገ መልኩ የዩኒቨርሲቲዎቹ ማህበረሰብ አባላት ተሳትፈውበት እንዲመረጡና እንዲሾሙ ማድረግ፤ አነስተኛው ሶስት ዓመት የነበረውን የዩኒቨርሲቲ ትምህርት እርዝማኔ ወደ አራት ዓመት በማሳደግ የአንድ ዓመት የፍሬሽማን ፕሮግራምን በሥርዓተ ትምህርቱ ማካተት፤ በዩኒቨርሲቲዎች በመሰጠት ላይ የሚገኙትን ፕሮግራሞች በመገምገም የማጣጣም ሥራ፤ ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና በትኩረት እንዲለዩ ማድረግና ወደ ተለዩባቸው የትኩረት መስኮች እንዲሸጋገሩ የሚረዳቸው የትግበራና የሽግግር እቅድ ማዘጋጀት፤ በዩኒቨርሲቲዎች ለመማር ማስተማር፣ ምርምርና ጥናት፣ ተቋማዊ አስተዳዳር እና የወል አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶችን ማጥናት፤ በተደረገው የትኩረትና ተልዕኮ ልየታ መሰረት ጉድለቶችን ለመሙላት መስራት፤ ተጨማሪ ዩኒቨርሲቲዎችን የማስፋፋት ስራን ለጊዜው መግታት፤ ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ራስ-ገዝነት እንዲሸጋገሩ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምን ስልት መከተል እንደሚያስፈልግ መለየት፤ ለሁሉም የቅድመ ምረቃ ድግሪ ፕሮግራሞች የመውጫ ፈተና መተግበር፤ እንዲሁም፣ በኢንዱስትሪዎችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ ትስስርና ትብብር እንዲኖር መስራት እና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ከተቋሙ ተለቅቀው የነበሩ ጥናታዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ የጥናቱን ውጤትም Springer የተባለው ዓለም አቀፍ አሳታሚ ድርጅት (https://link.springer.com/book/10.1007/978-3-658-39082-2 ድረ-ገጽን ይጎብኙ) በቅርቡ በመጽሐፍ መልክ አትሞታል። ይህን አገራዊ ጥናት መሰረት በማድረግ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተልዕኮና የትኩረት መስክ ልየታ (Differentiation) በማድረግ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ተግባር መግባታቸው ይታወሳል።

እንደ ትምህርት ሚኒስቴር እምነት፣ ቀደም ሲል የነበረው የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች አደረጃጀትና ትግበራ ተጨባጭ በሆነ ሀገራዊና ክልላዊ ፍላጎት ጥናትን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የሚመረቀውና የሚፈለገው የሰው ኃይል ሊጣጣም አልቻለም፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ግቦች ለማሳካት ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና የትኩረት መስክ ለይተው ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

* የሚከፈቱ የትምህርት ክፍሎችና ፕሮግራሞች የዩኒቨርሲቲዎችን ውስጣዊ አቅም (የመምህራን፣ ትምህርት ግብአቶች፣ መሰረተ ልማትና ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶችን ያማከሉ ያሟሉ ለማድረግ)፤
* ዩኒቨርሲቲዎች አካባቢዊ ጸጋን መሰረት አድርገውና ተጠቅመው የመስራት ባህላቸው ለማሳደግ፤
* ዩኒቨርሲቲዎች ባላቸው ነባራዊ የትኩረት መስክ ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ ለማስቻል፤
* ከተለመደውና ባህላዊ ከሆነው የአደረጃጀትና ትግበራ ለመላቀቅ ፤
* ዩኒቨርሲቲዎች ከሚታይባቸው የትምህርት ክፍሎችና ፕሮግራሞች መደጋገምና መደራረብ ለማላቀቅ፤
* ደረጃውን የጠበቀ የመማር-ማስተማር ሂደት ለማስፈን፤
* አስፈላጊ የሆኑና የተመረጡ የትምህርት ክፍሎችና ፕሮግራሞች ላይ በማተኮር እንዲጠናከሩ ለማስቻል፤
* የሚከፈቱ የትምህርት ክፍሎችና ፕሮግራሞች ሀገራዊና ክልላዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማስቻል በዋነኝነት የተመላከቱ ጉዳዮች ናቸው።



አቶ ሰይድ መሀመድ

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተልዕኮና የትኩረት መስክ ልየታ አስፈላጊነትና በዩኒቨርሲቲዎች ለትምህርት ጥራት ያለውን አስተዋፅኦ አስመልክቶ በተዘጋጀውና ይፋ በተደረገው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንደ ሰፈረው፣ ዩኒቨርሲቲዎች በተልዕኮና ትኩረት መስክ ተለይተው ወደ ትግበራ መግባታቸው የትምህርት ጥራትን ከማስጠበቅና አለማቀፋዊነትን ከማረጋገጠ አኳያ አዎንታዊ ለውጦች እየተመዘገቡ ነው፡፡ በዚህም የተደጋገሙና ተመሳሳይ የሆኑ የትምህርት ክፍሎችና ፕግራሞችን የማጠፍ፤ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑትን ደግሞ የማስፋትና የማጠናከር፤ አማራጮችን የማስፋት፤ ያለውን ሀገራዊ እና ክልላዊ ፍላጎት መሰረት የማድረግ፤ የአቅም ግንባታና ሌሎች የማደራጀት ስራዎች በትኩረት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ተልዕኮና የትኩረት መስክን ለይቶ መፈጸምን በተመለከተ ተቋማቱ ግንባር ቀደም ሆነው እንዲወጡ፤ ተቋማዊ ነጻነታቸው እንዲጎለብት፤ እንዲሁም በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎቻቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ፋይዳው የጎላ መሆኑን በትግበራ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በትግበራ ወቅት በትምህርት ማህበረሰቡ በኩል አልፎ አልፎም ቢሆን ተገቢ ያልሆኑ ስጋቶች እየተስተዋሉ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል የሚለው የሚኒስቴሩ የወቅቱ መግለጫ፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዩኒቨርሲቲዎች በተልዕኮና የትኩረት መስክ ለይተው ወደ ተግባር መግባታቸው ለዩኒቨርሲቲውም ይሁን ለአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ እድል እንጂ ስጋት የሚሆንበት ጉዳይ የለም በማለትም አስፍሯል፡፡

በተለይም ከላይ ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና ትኩረት መስክ መለየት ያስፈለገበት ዝርዝርና ምክንያታዊ እሳቤዎች በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን፤

እነዚህን ጥናታዊ ተግባራትና አስተያየቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰሩ ስራዎች በተለመደው መልኩ ይቀጥላሉ ማለት ሳይሆን ምቹ የሆነ አደረጃጀት ፈጥሮ መጠቀም እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ትግበራው ትምህርት ሚኒስቴር ባስቀመጠው የትግበራ ስትራቴጂ መሠረት እየተፈጸመ ያለ ሲሆን፣ በተቋማቱ ሲተገበሩ የነበሩ፤ ነገር ግን የዩኒቨርሲቲዎቹ ትኩረት መስክ የማይሆኑ ፕሮግራሞች ቢያጋጥሙ በሌሎች አማራጮች የሚቀርቡበት እድል ዝግ አይደለም የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና ብቃት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ የሆኑት አቶ ሰይድ መሀመድ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደተናገሩት ከሆነ፣ የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች ተልዕኮና የትኩረት መስክ ልየታ ማሳያ በጥናቱ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች ከሚኖራቸው ዓለም-አቀፋዊ፣ ሀገራዊና ክልላዊ ጠቀሜታ አንጻር ከዚህ በሚከተሉት ዋና ዋና ተልዕኮዎች ተለይተዋል።

1. የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች (Research Universities)
2. አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች (University of Applied Sciences)
3. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች
4. አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች (Comprehensive Universities) ሲሆኑ፣ በ2014 አንድ ተጨማሪ ልዩ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ (ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ) እንዲለይ ሆኗል።

በላይኛው ልየታ መሰረት (ዝርዝሩን ከሌሎች የተቋሙ ሰነዶች ነው ያገኘነው)፣ 1. አዲግራት ዩኒቨርሲቲ 2. ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ 3. ቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ 4. ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ 5. እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ 6. ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ 7. ደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ 8. ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ 9. ጂንካ ዩኒቨርሲቲ 10. ቀብሪድሃር ዩኒቨርሲቲ መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ 12. መቅደላምባ ዩኒቨርሲቲ 13. መቱ ዩኒቨርሲቲ 14. ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ 15. ኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ 16. ራያ ዩኒቨርሲቲ 17. ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ 18. ወራቤ ዩኒቨርሲቲ 19. ወልድያ ዩኒቨርሲቲ 20. ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ 21. ቦረና ዩኒቨርሲቲ በ"አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች፡፡

1. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 2. ጅማ ዩኒቨርሲቲ 3. ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 4. ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ 5. ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ 6. ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ 7. መቀሌ ዩኒቨርሲቲ 8. አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ በ"የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች።

አምቦ ዩኒቨርሲቲ 2. አርሲ ዩኒቨርሲቲ 3. አሶሳ ዩኒቨርሲቲ 4. አክሱም ዩኒቨርሲቲ 5. ዲላ ዩኒቨርሲቲ 6. ድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ 7. ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ 8. ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 9. ወሎ ዩኒቨርሲቲ 10. ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ 11. ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ 12. ሰመራ ዩኒቨርሲቲ 13. ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 14. ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ 15. ወለጋ ዩኒቨርሲቲ በ"የተግባር ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች ስር፤ እንዲሁም፡፡

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በ"ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች (STUs) ስር እንዲያርፉ ተደርጎ የመማር ማስተማሩ ስራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና ብቃት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊው አቶ ሰይድ መሀመድ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደ ተናገሩት ይህ ልየታ ያስፈለገው ከትኩረት መስክና ተልእኮ አኳያ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት የነበረው የመማር-ማስተማር ሁኔታም ይሁም የዩኒቨርሲቲዎቹ አደረጃጀት ከተልእኮና የትኩረት መስክ አኳያ ሳይሆን ሁሉም አንድ አይነት የትምህርትና ጥናት መስኮችን የሚያቀርቡበት፤ ተመሳሳይ የትምህርት ፕሮግራሞችን የሚሰጡበትና የአገርና ሕዝብ ፍላጎቶችን ያላገናዘቡ ነበሩ። በመሆኑም ይህ ልየታ አስፈልጓል። በልየታው መሰረትም በጥልቅ ጥናትና ተግባር ላይ የተመሰረተ የተቋማቱ ድልድል ተከናውኗል።

ኃላፊው እንደነገሩን ከሆነ ከ2014 ዓ·ም ጀምሮ ሲጠና የነበረው መሰረታዊ ጉዳይ፣ በልየታው መሰረት በዚህ ዓመት ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን፣ የየተቋማቱ ስርዓተ ትምህርቶችም (ካሪኩለም) በዚሁ መሰረት እየተዘጋጁ ይገኛሉ። ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በልየታው መሰረት ካላቸው ማንነት አኳያ የየራሳቸውን ስርዓተ ትምህርት በመከለስ በማዘጋጀት ላይ ናቸው።

አቶ ሰይድ እንደሚሉት፣ በተልእኮና ትኩረት መስክ ከመደራጀት አኳያ የቀድሞዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች የተሻሉ ነበሩ። ለምሳሌ እርሻ ወይም ግብርና ሲባል በእያንዳንዳችን አእምሮ ውስጥ የሚመጣው የቀድሞው አለማያ የዛሬው ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ነበር። አንድ ተማሪ ውሀ ቴክኖሎጂን ለማጥናት ካሰበ አስቀድሞ በአእምሮው የሚመጣው አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እንጂ ሌላ አይደለም። ሌሎቹንም በዚሁ መልክ ማሰብ ይቻላል። ስያሜያቸው ራሱ ይናገራል። አሁን ግን ያ የለም። ሁሉም ሁሉንም ይሰጡ ዘንድ የተቋቋሙ ናቸው። የየራሳቸው ልህቀት (ኤክሰለንስ) የላቸውም። ያ ደግሞ የሚያስኬድ ባለመሆኑ በሪፎርሙ (ለውጡ) እንዲታይ ተደርጓል። በተልእኮና ትኩረት መስክ መለየቱ አስፈላጊ ስለሆነም ነው ወደ እዚህ አሰራር መምጣት የተፈለገው። ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱም እንደዛው።

ሌላው በዚሁ በ2016 ወደ ተግባር የተገባበት ጉዳይ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና (GAT) ሲሆን፣ እንደ አቶ ሰይድ ማብራሪያ ተግባሩ በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል። ተቀባይ ተቋማትም የየራሳቸውን ፈተና በመስጠት ተፈላጊውን ውጤት ያመጡትን እየተቀበሉ በማስተማር ላይ ናቸው።

ለረዥም ጊዜ ሲጠና የቆየውና ዘንድሮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወደ ስራ የተገባበት የራስ ገዝ (ኦቶኖሚ) አወቃቀር ሲሆን፣ ወደ ፊት ሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ወደዚሁ ራስ ገዝ አወቃቀር እንዲገቡ እንደሚደረግ አቶ ሰይድ ተናግረዋል።

ለመጀመሪያ ጊዜ ባለፈው ዓመት የተጀመረው የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች የመውጫ ፈተናም በዚህ ዓመትም ቀጥሎ የተማሪዎች ውጤትና ለፈተናው እያደረጉት ያለው ዝግጅት እየተሻሻለ በመምጣት ላይ መሆኑን ኃላፊው አስረድተዋል። ይህ "ለመጀመሪያ ጊዜ ቢባልም፣ የመውጫ ፈተናው ድሮ ለሕግና ለህክምና ተመራቂዎች ይሰጥና ውጤታማ ስራም እንደ ነበር አስታውሰዋል።

በአጠቃላይ፣ ትምህርት ሚኒስቴር በ"አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ስም ከመሰረቱ የተበላሸውን የአገሪቱን የትምህርት ስርዓት ከመሰረቱ ለማሻሻል በርካታ የማሻሻያና የለውጥ ስራዎችን ሲሰራ መቆየቱን ስንገልፅ መቆየታችን ይታወቃል። ዛሬም ከላይ የጠቀስናቸውና መሰረታዊ ለውጦች የሆኑትን፣ ጥቂቶቹን ይዘን መቅረባችን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችል ነው። ወደ ፊትም ሌሎች ከለውጡ (ሪፎርም) ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ስራዎችን ይዘን የምንቀርብ መሆናችንን በመግለፅ የዛሬውን ዝግጅታችንን እናጠናቅቃለን።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ገዳዮችን የመውደድ የፖለቲካ ባህላችን መለወጥ አለበት››

**የተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አንጋፋው ፖለቲከኛ ዲማ ነገዎ (ዶ/ር)**



ምሕረት ሞገስ

በ1965 ዓ.ም ከቀድሞ ቀዳማይ ኃይለስላሴ ከአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስ እና በመንግስት አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ በጊዜው የመጨረሻው የንጉሱ ዘመን የድግሪ ተመራቂ ሆነው ከንጉሱ እጅ ሽልማታቸውን ተቀብለዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተማሪ ሕብረት ላይ ከመሳተፍ በተጨማሪ ትምህርታቸውን በትጋት እየተከታተሉ ኦነግን ለመመስረት ከእነ ሌንጮ ለታ ጋር ብዙ ሠርተዋል፡፡ እስከ አሁን ድረስም በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል የፖለቲካ ትግል ውስጥ በመሳተፍ ከግንባር ቀደሞቹ መካከል ተጠቃሽ ሆነዋል፡፡

የኦነግን የፓርቲ ፕሮግራም ከመቅረፅ ጀምሮ ሴሎችን በማደራጀት ለፓርቲው መመሥረት ሠፊውን ሚና ተጫውተዋል፡፡ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ንቃት ተከታትለው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በከፍተኛ ውጤት ቢያጠናቅቁም ሥራ ማግኘት ቀላል አልሆነላቸውም። ከእርሳቸው በታች ነጥብ ያስመዘገቡ ተመራቂዎች በጊዜው ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎችም ከእርሳቸው ሞያ ጋር የተያያዘ ሥራ የሚያሠሩ ተቋማት ውስጥ ሲቀጠሩ እርሳቸው ግን ማንም ሊቀጥራቸው ፈቃደኛ አልሆነም ነበር፡፡

ሳይታክቱ የተለያዩ ተቋማት እየሄዱ ቢያመለክቱም ሥራ አላገኙም፡፡ ሥራ ያጡባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም፤ ዋነኛው ግን የመመረቂያ አጠቃላይ ነጥባቸው ታይቶ፤ የፅሁፍም ሆነ የቃል ፈተና ተፈትነው ሁሉንም ካለፉ በኋላ፤ የመመረቂያ ፅሁፋቸውን ሲጠየቁ የሚያቀርቡት የወቅቱን የመሬት ሥርዓት አካሔድ ትክክል አለመሆኑን የሚያመላክት በመሆኑ በተቋማት ለመቀጠር ተቸገሩ፡፡ ለስምንት ወራት ሥራ አጥተው ቢንከራተቱም፤ ሥራ አለማግኘታቸው ግን በሌላ በኩል ኦነግን በደንብ ለማደራጀት ዕድል ሰጣቸው፡፡

በኋላም ወደ ወለጋ ሥራ አግኝተው እንደሄዱ ብዙም ሳይቆዩ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በሕዝብ ትግል ስልጣናቸውን ለቀቁ፡፡ ደርግ መምጣቱን ተከትሎ እርሳቸው የመሬት አስተዳደር ሥራ ላይ በመሠማራት ጭሰኛው የመሬት ባለቤት እንዲሆን በመስራት መሬት ላራሹን በፈለጉበት መንገድ እንዲተገበር ከጓደኞቻቸው ጋር ከፍተኛውን ሚና ተጫወቱ፡፡

ቀጥለው ደርግ የእርሳቸውን እና የኦነግን ፍላጎት መፈፀም እንደማይችል በመገንዘብ የኦነግ ጦርን ለማጠናከር ሱዳን እና ኤርትራ ድረስ ሔደው ብዙ ሥራዎችን ሰርተዋል። የኦነግ መስራች እና የመጀመሪያው የፓርቲው ፕሬዚዳንት የዛሬው የወቅታዊ እንግዳችን ዲማ ነገዎ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

በጫካ ሲታገሉ ቆይተው ደርግ ሲወድቅ፤ ኢህአዴግ ሙሉ ለሙሉ በደርግ እግር ተተክቶ አገር ማስተዳደር ከመጀመሩ በፊት በነበረው የሽግግር ጊዜ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሚንስትር ሆነው ሠርተው ነበር፡፡ በኋላም በነበረው የፖለቲካ ሴራ ተሰደው በውጪ ከቆዩ በኋላ፤ ከአምስት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ በተደረገው የመንግሥት ለውጥ በስደት ከሚኖሩበት አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት፣ ይመሩት የነበረውን የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር በመተው፤ በስድስተኛው አገራዊ ምርጫ በግል ተወዳድረው በማሸነፍ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። ሰላም ላይ በማተኮር እየተደረገ ያለውን ጥረት እና አጠቃላይ የወቅቱን የአገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ እንዲሁም ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለችውን ሀገራዊ ምክክር በተመለከተ ከእኒሁ አንጋፋ ፖለቲከኛ ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ጉዳት እያስከተሉ ካሉ የተለያዩ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛው በጦርነት አልሸነፍም በማለት ከመነጋገር እና ተደራድሮ ችግርን ከመፍታት ይልቅ በስሜት ወደ ጦርነት እና ግጭት ፊትን ማዞር የተለመደ ስለመሆኑ ይነገራል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** ከመንግስት አንፃር ካየነው ይህ በየትኛውም ዓለም ያለ የመንግስት ፀባይ ነው። ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ማንኛውም መንግስት ‹‹ሁሉንም ኃላፊነት የምወስደው እኔ ነኝ፡፡ ማሸነፍ እና ማንበርከክ እችላለሁ›› ብሎ ይገምታል፡፡ በእርግጥ መንግስት ማንበርከክ ይችላል። ነገር ግን ቢችልም አገሪቱ ትጎዳለች። ሕዝብ ይጎዳል፡፡ ስለዚህ የግድ አንዳንድ ነገሮችን ተቀብሎ ለሰላም መድረኩን መክፈት እና ለሰላማዊ አማራጭ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

የመንግስት ኃላፊነት ከሁሉም አንፃር የሚታይ ነው። ይህ እስከ ሆነ ድረስ ማሸነፍ እና ማንበርከክ እችላለሁ ብቻ ብሎ በማመን የኃይል አማራጭን ብቻ እንደመፍትሔ መውሰድ ከመንግስትነት አንፃር ተገቢ አይሆንም፡፡ ለመፍትሔ የኃይል አማራጭ ብቻውን በቂ አይሆንም። በፖሊስ ብቻ አገር አይመራም፡፡ የፖለቲካ ቅቡልነት ለማግኘት ሕዝቡን የግድ በሰላማዊ መንገድ ማሳመን ያስፈልጋል፡፡ የሚያዋጣው ኃይል ሳይሆን ተቀባይነት የሚገኝበትን መንገድ መፈለግ ነው።

ሌላው ታጣቂም በመሳርያና በግጭት ለውጥ አመጣለሁ ብሎ ከማሰብ መራቅና በውይይትና በምክክር ዓላማን ከግብ ማድረስ እንደሚቻል ሊረዳ ይገባል፡፡

**ቡድን ፈጥረው የፖለቲካ ዓላማቸውን በመሳሪያ ኃይል ለማስፈጸም የሚታገሉ ቡድኖች የቀድሞ አካሄዳቸውን ትተው በሰላማዊ መንገድ ለመኖር እና ለመታገል እምነት ሊያድርባቸው ይገባል**

**አዲስ ዘመን፡- የፌዴራል መንግስት በተደጋጋሚ ሠላም ለማምጣት ጥረት አድርጓል፡፡ ለምሳሌ ከሕወሓት ጋር ያካሄደውን የፕሪቶሪያውን ስምምነት መጥቀስ ይቻላል። እንደውም ስምምነቱን ተከትሎ ብሔራዊ የተሃድሶ ኮሚሽን አቋቁሟል፡፡ ኮሚሽኑ ከሌሎችም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እየተወያየ እየሠራ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** በአገሪቱ ካሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ከዚህ በፊትም ውይይት ይደረጋል፡፡ አሁን ደግሞ በዚህ ጉዳይ ላይ የልዩ ልዩ አገሮችን ተሞክሮ እና ልምድ ለማግኘት እና የወደፊቱ የአገራችን ዕጣ ምን ይሆናል? የሚለው ላይ ከፓርቲዎች ጋር ውይይት ለማድረግ ጥሩ ጅማሮ እየታየ ነው፡፡ ይህ በመንግስት በኩል ብቻ የሚሠራ ሥራ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ማህበራዊ ተቋማትም አስተዋፅኦ ያስፈልጋል፡፡ የእነርሱንም ሃሳብ መውሰድ ጥሩ ነው፡፡

በእርግጥ የተሃድሶ ኮሚሽን የተቋቋመው የሰሜኑን ጦርነት ያቆመውን የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተከትሎ ነው። ጦርነት ከቆመ በኋላ ታጣቂ የነበሩ ሰዎች ወደ ሕብረተሰቡ መመለስ አለባቸው ዋናው ተግባሩ ይህንን ማድረግ ነው። ስለዚህ ብሔራዊ የተሃድሶ ኮሚሽን ማለት መጀመሪያ ጦርነቱ ውስጥ ገብተው የነበሩትን ተቀናጅተው የሚዋጉትን እንዳይዋጉ መሳሪያ ፈተው ወደ ሕብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ማድረግ የእርሱ ተግባር ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የፖለቲካ ፓርቲዎች ለብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ምን መሆን አለበት ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** እነዚህ ተደራጅተው ቡድን ፈጥረው ለፖለቲካ ዓላማቸውን በመሳርያ ኃይል ለማስፈጸም የሚታገሉ ቡድኖች የቀድሞ አካሄዳቸውን ትተው በሰላማዊ መንገድ ለመኖር እና ለመታገል እምነት ሊያድርባቸው ይገባል፡፡ አሁን ባለው የፖለቲካ ሥርዓት እምነት እንዲያድርባቸው የመንግስት ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ እምነት በማሳደር በኩል የእነዚህ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሚና ቀላል አይሆንም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአጠቃላይ በአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎ ምን መሆን አለበት?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** እውነት ለመናገር በአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ ለማለት አልደፍርም። በአገራችን የፖለቲካ አደረጃጀት የተጀመረው በ1970ዎቹ ነው። የተጀመረበትም ሁኔታ ሕዝብን በግልፅ አደራጅቶ ለፖለቲካ ዓላማ ለማሰለፍ ሳይሆን በድብቅ ተደራጅቶ የፖለቲካ ዓላማን ለማራመድ ነው። አደረጃጀቱ በጫካ ወይም በድብቅ በከተማ ነበር። የመጀመሪያዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በእዚህ መልክ መደራጀታቸው ለፖለቲካ ፓርቲዎች በበቂ መጠን አለመጠናከር የራሱን አሉታዊ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ሌላኛው ደርግ የመጀመሪያው ያቋቋመው የፖለቲካ ፓርቲ ነው፡፡ ደርግ አስር ዓመት ሥልጣን ላይ ወጥቶ ከተቀመጠ በኋለ ፓርቲ አደራጀ፤ ብዙም ሳይቆይ ወደቀ፡፡ ያ ፓርቲ ዛሬ የለም፡፡ ሕዝባዊ ሳይሆን መንግስታዊ ፓርቲ ነበር ማለት ነው፡፡ እነዚህ ልምዶች በአገራችን የፖለቲካ ፓርቲ እድገት ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ አሳርፈዋል፡፡ ወደ ፊት የፖለቲካ ምህዳሩ እየሠፋ የሕዝቡም ፍላጎት እና ንቃተ ህሊና እያደገ ሲሔድ፤ ከዚህ በተሻለ መንገድ በሰፊው ሕዝብ ላይ የተመሠረቱ ፓርቲዎች ወይም በፖለቲካ ዓላማ የተደራጁ ግለሰቦች እና ፓርቲዎች እየተጠናከሩ ይሔዳሉ ብዬ እገምታለሁ።

አሁን የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖች አሉ፡፡ እነዚህ ቡድኖች መንግስት ውስጥ የሌሉት፤ ሥራቸው ስለመንግስት ማማረር ነው፡፡ መንግስት ይህን አላደረገልንም፤ የፖለቲካ ምህዳሩን ክፍት አላደረገም ይላሉ፡፡ መቼም ቢሆን ፖለቲካ ውስጥ መግባት መስዋትነትን ይጠይቃል፡፡ በፖለቲካ ትግል ውስጥ መግባት ብዙ መስዋትነት ያስከፍላል፡፡ መስዋትነትን ፈርቶ ትግል ማድረግ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ የግድ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ ከጠቀሷቸው ምክንያቶች በተጨማሪ ሁሉንም ሊገዛ የሚችል የፓርቲ ፕሮግራም ይዘው አለመምጣታቸው በፓርቲዎች ዕድገት ላይ የፈጠረው ተፅዕኖ የለም?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** አዎ! ነገር ግን አሁን የፖለቲካ አመራር ላይ ያሉትን ብዙዎቹን ሰዎች ብንወስድ ላለፉት ሰላሳ እና አርባ ዓመታት የነበሩ ሰዎች ናቸው። ብዙ አይለወጡም፤ እየተተካኩ አይሄዱም። እንደማስበው ከመጀመሪያው ጀምሮ የሆነ ውስንነት አለ፡፡ ውስንነቱ በአጠቃላይ አገሪቱን እና ሕዝቡን የተመለከተ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጥ የሚያመጣ ፕሮግራም ነድፈው ዓላማቸውን ለማሳካት ሕዝብን ምን ያህል አንቀሳቅሰዋል? ምን ያህልስ አባል አላቸው? የሚለው ወሳኝ ነው።፡ አሁን እያንዳንዱ ፓርቲ ምን ያህል አባል አለው መልሱ ያጠያይቃል፡፡ ብልፅግና 14 ሚሊየን የፓርቲ አባል አለኝ ይላል፡፡ ያን ያህል ቁጥር ያለው አባልን በዲሲፕሊን በአንድ ፕሮግራም እየመራ ነው ወይ የሚለው ግራ ያጋባል፡፡ ነገር ግን ሲበዛም ጥሩ አይደለም፡፡

በምርጫ ቦርድ ፓርቲዎች 10 ሺህ ወይም 20ሺህ አባል ሊኖራቸው ይገባል ሊል ይችላል፤ ምርጫ ቦርድ በሚያስቀምጠው የአባል ቁጥር መጠን 120 ሚሊየን ሕዝብ ባለበት አገር ውስጥ 100 ፓርቲ ማቋቋም ይቻላል፡፡ ነገር ግን በእኔ እምነት ፓርቲ ፓርቲ መሆኑ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

# ‹‹ገዳዮችን የመውደድ የፖለቲካ...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

የሚታወቀው በምርጫ ተፈትኖ ነው፡፡ ይሔ ፓርቲ ስንት መቀመጫ አገኘ ሲባል ይፈተናል። በፌዴራል ምክር ቤት ውስጥ ከ12 አባላት ውጪ ሁሉም መቀመጫዎች የገዢው ፓርቲ ናቸው፡፡

እነዚህ 12 መቀመጫዎች ትንሽ እየበዙ፤ ፓርቲዎች እየጠነከሩ ከሔዱ፤ የሌሎች ፓርቲዎች አደረጃጀት እየተጠናከረ ሊሔድ ይችላል፡፡ አንዳንዴ ተመሳሳይ ፓርቲዎች አሉ፡፡ ብዙ ከሚሆኑ እየተዋሃዱ እና አንዱን እያጠናከሩ መሔድ ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በተለይ ሰላም ላይ በማተኮር እየተደረገ ያለውን ጥረት እና አጠቃላይ የወቅቱን የአገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** የሰላም ስምምነት ተካሂዶ የሰሜኑ ጦርነት ካበቃ በኋላ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በተወሰነ መልኩ ሠላም ተስተውሏል፡፡ ስምምነት መፈጠሩ በራሱ ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡ የብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን መቋቋሙም መልካም ነው። እንዲህ ዓይነት የሰላም ስምምነት ሌሎቹንም እያካተተ በአጠቃላይ በአገሪቱ ሰላማዊ የሆነ የፖለቲካ ሕይወት ይኖራል የሚል ተስፋ እየታየ ነው፡፡ በእኔ እምነት መልካም የሰላም ሁኔታ አለ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የትግራይ በስምምነት ቢቋጭም በአማራም ሆነ በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ግጭት ይስተዋላል፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ምን ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** በአንፃራዊነት ስንመለከተው በሰሜኑ ክልል በትግራይ አካባቢ የነበረው ጦርነት በሁለት ጦሮች መካከል የተካሔደ ነበር፡፡ ለእዛውም አንድ ጦር የነበረ ማለትም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የነበረ ለሁለት ተከፍሎ እርስ በእርስ ውጊያ ላይ መቆየታችን የሚካድ አይደለም። ያ ጦርነት ከባድ ነበር፡፡ ብዙ ሰው ተሳትፏል፤ ጉዳቱም በሁለቱም በኩል ቀላል አልነበረም። ይህ ማለት ግን በዛ ጊዜም ቢሆን በሌሎች አካባቢዎች ሰላም ነበር ማለት አይደለም፡፡

በአንፃራዊነት ስናየው በተለያዩ አካባቢዎችም ግጭቶች ነበሩ፡፡ ግጭቶቹ አሁንም የሚታዩ ሲሆኑ፤ መልካቸውን እየቀያየሩ የሚሔዱበት ሁኔታ አለ። ስለዚህ በተቻለ መጠን እነዚህ ግጭቶች ሰላማዊ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ በዋናነት ኃላፊነቱን ሊወስድ የሚገባው መንግስት ነው። መንግስትም ጥረት እያደረገ ይመስለኛል፡፡ መንግስት በኦሮሚያ ክልል አካባቢ ያለውን ችግር ለመፍታት አንድ ሁለቴ ድርድር ለማድረግ መሞከሩን እናውቃለን፡፡ ከዚህ በኋላም ድርድሩ ይቀጥላል፤ ቀጥሎ ወደ እልባት ይደርሳል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥ መንግስት ለድርድር በሩ ክፍት መሆኑን እየገለፀ ይገኛል። በተቃራኒው ደግሞ በትግራይ ክልል ዙሪያ የነበረውን ጦርነት በድርድር ማስቆም ቢቻልም፤ በኦሮሚያ ክልል ለሚስተዋለው ችግር ግን የተሳካ ውይይት እንዳልተካሔደ ታውቋል። በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** መንግስት የሚጠበቅበትን አንዳንዴም አልፎ እየሔደ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት። መንግስት ተቃዋሚው እምነት እንዲያድርበት ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ሲያደርግ ዛሬ መሳሪያ አንስተው ጫካ የገቡትም እምነት አድሮባቸው መሳሪያቸውን ጥለው ‹‹ነገ የማምንበትን ዓላማ በሠላማዊ መንገድ ላካሄድ እችላለሁ›› ብለው ከህብረተሰቡ ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ ይህን የመሰለ እምነት ላይ እንዲደርሱ መንግስት አሠራሩን ሊያይ እና ሊያሻሽል ይገባል፡፡ አያያዙ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን በሚያሳምን መልኩ መሆን አለበት፡፡

መሳርያ ያነሱትም ቢሆኑ በውይይት ማመን አለባቸው። መሳርያ አንስቶ ውጤት ማምጣት እንደቀድሞው አዋጭ ላይሆን ይችላል፡፡ ዋናው ነገር ተቀራርቦ ለመስራት መሞከር ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለአገር ዘላቂ ሰላም ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ተቋቁሟል፡፡ በብሔራዊ ምክክር ዙሪያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋነኛ ዓላማው የአገሪቱን ዋና ዋና ችግሮች ከዚህ በፊት



**ስምምነት መፈጠሩ በራሱ ተስፋ የሚሰጥ ነው። የብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን መቋቋሙም መልካም ነው**

አንዳንዶች ትጥቅ ያነሱባቸው ጉዳዮችን በምክክር መድረክ እልባት ሰጥቶ ወደ በለጠ ሰላማዊ የፖለቲካ ሕይወት አገሪቱን መምራት ነው፡፡ ውይይቱ ዋና ዋና አጨቃጫቂ በሆኑ ጉዳዮች ሲሆን፤ ለምሳሌ ሕገመንግስቱ ይቀየር የሚሉ ሰዎች አሉ። ይቀየር ብለው ጠመንጃ ያነሱ ሰዎች ቢኖሩም፤ የለም መቀየር የለበትም ብለው የሚከራከሩም አሉ፡፡ መጀመሪያ ይቀየር የሚለው ላይ መስማማት ያስፈልጋል፡፡ ከዛም ምን ምን ዓይነት ቦታ ላይ ይቀየር? የሚለው ላይም መግባባት ያስፈልጋል፡፡ ድርድር የሚያስፈልገው ለእዚህ ነው፡፡

ምክክሩ በኋላ ወደ ድርድር ይሔዳል፡፡ እኔም የተወስነ የምሠጠው አለ፤ ሌላውም የሆነ የሚሠጠው ነገር ይኖረዋል። እኔ ያልኩት ብቻ ሊሆን አይችልም። ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ናት። ብዙ ፍላጎቶች አሉ። በብሔር እና በሃይማኖት ብቻ አይደለም፡፡ በዕድሜ፣ በፆታ፣ በሥራ ለምሳሌ አንዱ አራሽ ሲሆን፤ ሌላው ከብት አርቢ ነው፤ በዚህ እና በሌሎችም በብዙ ጉዳዮች ልዩነቶች ይኖራሉ። ሁላችንንም የሚያስማማን ነጥብ ላይ መድረስ ይኖርብናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በብዙ ጦርነት እና ግጭቶች ውስጥ አልፈናል፡፡ በእዚህ በድህረ ጦርነት ማግስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለአገር ሰላም እና ዕድገት ምን ማድረግ አለባቸው?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** ዋነኛው ዓላማችን እና ምኞታችን ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊት አገር ማድረግ ነው። የፖለቲካ ሥርዓቱ ዴሞክራሲያዊ ሆኖ መንግስት ተጠያቂነት ያለበት የሚሆንበትን ሥርዓት መመሥረት ነው፡፡ ለእዚህ አንዱ ቁልፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖር ነው፡፡ የመንግስትን ተጠያቂነት ማረጋገጥ የሚቻልበት አንዱ ነፃ ፕሬስ፣ ነፃ ፍርድ ቤት እና ነፃ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመሳሰሉት መኖራቸው ወሳኝ ነው፡፡

ምኞታችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት በመሆኑ በዚህ ሂደት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ትልቅ ነው። ሕዝቡ ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሻለውን የመምረጥ እና የመጣል መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ ይሔ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከጥንት ጀምሮ በአብዛኛው በቡድን ብረት ይዞ ወደ ትግል የመግባት ዝንባሌ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በተደጋጋሚ ይታያል። ይህ እንዳይሆን ሕዝቡ መነጋገር ላይ እንዲያተኩር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** ይህንን ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው። እኛ ጋንዲ የለንም፡፡ የምናምነው እና የምንወደው ገዳይን ነው፡፡ በአመዛኙ ባህላችን በገዳዮች የሚያምን ነው። ገዳዮችን የመውደድ የፖለቲካ ባህላችን መለወጥ አለበት። ይህ እስካልተለወጠ ድረስ ምንም ማድረግ አንችልም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የፓርቲዎች እንቅስቃሴ እና የፖለቲካ ሁኔታ ሲነሳ የተቋማት አደረጃጀት እና ነፃነት ጉዳይ ይጠቀሳል፡፡ በዚህ ዙሪያ ምን ይላሉ?**

**ዶ/ር ዲማ፡-** እንደውም መጀመሪያ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲጠናከሩ፤ ተቋማት ገለልተኛ እና ሞያ ላይ የተመረኮዙ ለማንም የማይወግኑ መሆን አለባቸው። ተቋማት አንድ ፓርቲም ሆነ ማንኛውም ሰው ስልጣን ላይ ይኑር አይኑር ለማንም የማይወግኑ ተልዕኳቸው አገራዊ እና ሕዝባዊ ብቻ መሆን አለበት። ለምሳሌ የፍትሕ ተቋማት፣ መከላከያ፣ ደህንነትን የመሳሰሉት ተቋማት አገራዊ መሆን አለባቸው፡፡

ይሔ እየተደራጀ የሚሔደው በሒደት ነው። አሁን ላይ ካየናቸው አጀማመራችን ጥሩ ነው፡፡ ባለፉት ዓምስት ዓመታት ብዙ መሻሻሎች አሉ፡፡ ብዙ ለውጦች ተደርገዋል። ነገር ግን ይሔ እየተጠናከረ መሔድ አለበት የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ ሌላኛው በፓርቲ እና በመንግስት መካከል ድንበር መኖር አለበት፡፡ ይሔ ድንበር ካልተስተካከለ ለሌሎችም በፖለቲካው ዘርፍ ለሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ተስፋ እና አመኔታን ያሳጣል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ እናመሰግናለን፡፡**

**ዶ/ር ዲማ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የሀገር ባህል ልብስን ለአዘቦት ቀን

**ሰሚራ በርሀ**

አቤል ተስፋዬ ይባላል፡፡ በሀገር ውስጥ የሚሰሩ ልብሶችን በማምረት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ያከፋፍላል። የልብስ ዲዛይንም ያወጣል፡፡

እናት እና አባቱ በተሰማሩበት ሙያ እሱና ወንድሙም ተስበው የስራው አንድ አካል ሆነዋል፡፡ ወላጅ እናቱ አረጋሽ ተሾመ በጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ውስጥ ሰርተዋል፤ ይህን ልምዳቸውን ይዘው ሙሉ ለሙሉ በእዚህ የአልባሳት ሙያ ውስጥ ይሰራሉ፡፡ አባታቸው አቶ ተስፋዬ አበራም አስድቀድመው ይሰሩ ከነበሩት ስራቸው ወጥተው ሙሉ ለሙሉ ወደ ልብስ ዲዛይን ስራ ገብተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በልብስ ዲዛይን ትምህርት ቤት መምህር ናቸው ፡፡

አቤል ከቤተሰቦቹ በተቀበለው የልብስ ዲዛይን ስራና በሀገር ውስጥ አልባሳት ማምረት እየሰራ ይገኛል። ‹‹ኢትዮጵያውያን ማንኛውንም ነገር እዚሁ በሀገራችን አምርተን እንድንጠቀም እፈልጋለሁ›› የሚለው አቤል፣ ከአልባሳት እና ጨርቃጨርቆች ጋር በተያያዘም የራሳችን የሆነ ምርት ለምን አንጠቀምም የሚል እምነትም አለው ፡፡

የተለያዩ ሙከራዎችን በማድረግ የሀገር ውስጥ ምርትን በሀገር ልጅ በማለት የራሱን አስተዋጽኦ በጨርቃ ጨርቅ አልበሳት ላይ እያሳረፈ ይገኛል፡፡ የሀገር ባህል ልብስ መስሪያ ግብዓቶችን በመጠቀም ወጣ ያሉና ሰዎች በእለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ሊለብሷቸው የሚችሏቸውን ልብሶችን ይሰራል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ጋቢ የሚሰራበትን ‹‹ፈትል›› ጨርቅ በመጠቀም ለእለት ተዕለት አልባሳትነት የሚውሉ አልባሳትን በማምረት ወደ ገበያው ለማስገባት እያስተዋወቀ ይገኛል፡፡

ይህ ስራው በኢንተርፕራይዝ ደረጃ ከተቋቋመ ቆየት ቢልም፣ አቤል « 77 ልብስ ዲዛይን » የሚል ስያሜ የሰጠው የአልባሳት ስራ 2014 ዓ.ም ላይ ስራውን እንደ ጀመረ ይናገራል፡፡ ‹‹ምርቶቹን መጀመሪያ ቤት ውስጥ እየሰራሁ ለቤተሰቦቼ እና ለጓደኞቼ አለብሳቸው ነበር›› የሚለው አቤል፣ ተምሮ ከጨረሰበት እና ተቀጥሮ ይሰራበት ከነበረው



ስራ ይልቅ ከልጅነቱ ጀምሮ ቤት ውስጥ ይመለከተው የነበረውን የወላጆቹን ስራ በመምረጥ በተሻለ መልኩ በማሳደግ ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራው መግባቱን ያስታውሳል።

የሀገር ባህል ልብስ አልያም የጨርቃጨርቅ አልባሳት ስራ የብዙ እጅ ስራዎች እና ባለሙያዎች ውጤት መሆኑን ጠቅሶ፣ ይህንን ስራ ከባለቤቱ ሀና ታለጌታ ጋር በመሆን እየሰራ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ‹‹ባለቤቱ በሽመና ስራ እውቀቱ እንዳላት ጠቅሶ፣ የሽመና ስራውን ከሷ ከዲዛይን እና ከስፌት ጋር የተያያዘውን ደግሞ ከእኔ ጋር አድርገን እንሰራለን፡፡›› ይላል፡፡

ምርቱንም በሰፊው ለገበያ የማቅረብ ፍላጎት እንዳለው ጠቅሶ፣ የሀበሻ ልብስ የሚሰራበትን ግብዓት ለመስራት እና በሚፈለገው መልኩ ለመቆራረጥ ብዙ ሂደቶችን እንደሚያልፍ ይናገራል፡፡ ይህ ሁሉ ሁኔታ ጊዜ እንደሚወስድና በፈለገው ልክ ከመጓዝ እንዳገደው አመልክቷል፡፡

አቤል የሀገር ባህል አልባሳትን በፋብሪካ ደረጃ መስራት የወደፊት እቅዱ ነው፡፡ በዋናነት የሚጠቀመው ግብዓትም ‹‹ፈትል›› መሆኑን ይገልጻል፡፡ ጋቢ የሚሰራበት ባህላዊ ጨርቅ ሙሉ ለሙሉ ከጥጥ እንደሚመረት ገልጾ፣ በተለያየ ቀለማት የሚቀርበውን ‹‹ሱፍ›› ጨርቅ የሚባለውንም በግብዓትነት ይጠቀማል፡፡

‹‹የሀገር ባህል ልብሶች የተለየ ውበትን የሚፈጥሩ እና ሞገስን የሚያላብሱ ቢሆኑም፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት በብዙ ምክንያት እንዳይለመዱና አልባሳቱ በራሳቸው በኢትዮጵያውያን እንዳይዘወተር አደርጎታል›› የሚለው አቤል፣ የሀገር ባህል በተለየ መልኩ ቢሰራም በሚለበስበት ወቅት ጥንቃቄ ማድረግን እንደሚጠይቅ ይገልጻል፡፡ በዚህ የተነሳም ሰዎች በሀገር ውስጥ ለተሰሩ ምርቶች ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን አመልክቷል።

‹‹እንደ አጋጣሚም እንደ እድልም ሆኖ በአብዛኛው የኛን ምርቶች የሚጠቀሙት የውጭ ሀገር ዜጋዎች፣ በሀገር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ድምጻውያን ናቸው›› የሚለው አቤል፣ በሌላ ሀገር የሚገኙ ዜጎች አልባሳቱ የሀገር ባህል ልብሶች ከመሆናቸው ባሻገር በእጅ የተሰሩ መሆናቸው በራሱ ልዩ ስሜትን ይፈጥርላቸዋል ሲል ያብራራል፡፡

አቤል እነዚህን የሀገር ውስጥ እና ሌሎች ከሀገር ውጭ የሚመጡ ግብዓቶችን በመጠቀም ለእለት ተዕለት የሚሆኑ ሸሚዞች፣ ጃኬቶች እና የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ስራዎች የሚሆኑ እና በበጋ መለበስ የሚችሉ ልብሶችን እያመረተ ለገበያ ያቀርባል፡፡

የሀገር ባህል አልባሳት ኢትዮጵያን ከሚገልጹ እና ከሚያስተዋውቁ መገለጫዎቻችን መካከል ይጠቀሳሉ ያለው አቤል፣ ወቅትንና ፋሽንን በጠበቀ መልኩ እየተሰሩ መሆናቸውንም ይገልጻል፡፡ በሽመና እና በጥልፍ ስራው ላይ የምናስተውላቸው ባለሙያዎች በዘርፉ ረጅም ዓመት የሰሩ መሆናቸውን ጠቅሶ፣ ዘርፉ ጊዜውንም ያማከለ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች ራሳቸውን ማብቃትና የእውቀት ሽግግር ማድረግ እንደሚገባቸውም አስታውቋል፡፡

እሱ እንዳለው፤ ስራዎቹ ተፈላጊ እንዲሆኑ በተለያዩ ገበያዎች፣ ባዛሮች ላይ ምርቶቹን ይዞ ይቀርባል፡፡ በዚህም ራሱን ያስተዋውቃል፤ በዘርፉ ከተሰማሩ ሌሎች ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፡፡ በሀገር ልብሶች እና በሌሎች የአፍሪካውያን ጨርቆች የተሰሩ ቦርሳዎችም እያመረተ ለገበያ ያቀርባል፡፡

እሱ እንዳለው፤ የሀገር ባህል ልብሶች በሀገር ውስጥ አምርቶ ለመጠቀም ገበያው ገና አልተነካም ፡፡ የሀገሪቱ የጨርቃ ጨርቅ አልበሳት ዘርፍ በብዙ ሊሰራበት ይችላል። በጨርቃጨርቅ አልበሳት ዘርፉ ላይ በአብዛኛው የጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረት ይስተዋላል፡፡ በገበያው ላይ የሚገኙት ግብዓቶችም ቢሆኑ የሚሸጡበት ዋጋ ከጊዜ ጊዜ የሚለዋወጥ እና ውድ ናቸው፡፡

ጥራት ያላቸው ልብሶችን አምርቶ ወደ ገበያ ለማቅረብ በጥሬ እቃዎች ላይ የሚታየው የዋጋ ውድነት ተግዳሮት መሆኑን አስታውቋል፡፡ ይህ ችግር ልብሶቹ የሚሸጡበትን ዋጋ ከፍ እንዲል እንዳደረገውም ይናገራል፡፡

በጨርቃ ጨርቅ አልባሳት ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ሀገሪቱ ለውጭ ገበያ እንደምትልካቸው እንደ ቡና ያሉ ምርቶች ኢንዱስትሪው ደረጃውን የጠበቀ ኩባንያ ገንብቶ አልባሳትን በማምረት ምርቶቹን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተግዳሮት እንደሆነበት ጠቁሟል፡፡ የግብዓቶች ችግር ምርቱ ደረጃውን እንዳይጠብቅ እያደረገው መሆኑን ጠቅሶ፣ ይህ ችግር በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችም ከሀገር ውጭ ላሉ ደንበኞቻቸው የሚሆኑ ምርቶች ላይ እንዲያተኩሩ አድርጓቸዋል ይላል፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ጥምቀትን የሚያስታውሱኝ ሙስሊም አባት

**ዋለልኝ አየለ**

ከሦስት ዓመታት በፊት የጥምቀት ዕለት ነው። ከወሰን ወደ ሲኤምሲ ሚካኤል የሚወርደው ሰፊ አስፋልት መንገድ ግራ ቀኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ዓርማ ያለባቸው ባንዲራዎች ተሰቅለዋል፡፡ ከሰዓት፣ 8፡00 አካባቢ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ከሲኤምሲ ወደ ወሰን በሚወስደው አስፋልት በእግር እየወጣን ነው፡፡ ሰዓቱ ታቦታት ከማደሪያቸው ወደ መንበራቸው ገብተው መንገዶች ፀጥ ረጭ ያሉበት ነው፡፡ ድምቀቱ ያለው በቤተ ክርስቲያናቱ አካባቢ ነው፡፡ መንገዶች የሚደምቁት ምዕመኑ መመለስ ሲጀምር ነው፡፡

በዚህ ፀጥ ረጭ ባለ ጎዳና ላይ እየወጣን ሳለ ከላይ አንድ ሙስሊም አባት ወደ ታች ይመጣሉ፡፡ አንድ ቦታ ሲደርሱ ከመንገዱ ግራና ቀኝ ያሉ፣ ባንዲራ የተሰቀለባቸው ምሰሶዎች ወድቀዋል፡፡ ከላይ እየመጡ የነበሩት ሙስሊም አባት እነዚያን የወደቁ ምሰሶዎች እያነሱ፣ ከሥር በሚገኘው ማስደገፊያ እያስደገፉ ባንዲራዎችን ሲያቆሙ ተመለከትን፡፡

ሙስሊም ሆነው ይህን በማድረጋቸው ምንም አልገረመንም፡፡ አብሮኝ ያለው ልጅ አብሮ አደጌ ስለነበር እያየነው ያደግነው ነገር ነው፡፡ ከዚህ ጓደኛዬ ጋር አጀንዳ አድርገን እየተጨዋወትን የሄድነው የእንዲህ አይነት አባቶች ንጹህ ልቦና በብዙዎች ዘንድ የማይታወቅ መሆኑን ነው፡፡ ይህን እንድናስብ ያደረገን ደግሞ ለፖለቲካ ፍጆታ የሚደረግ ነው የሚባሉ ሰሞንኛ አጀንዳዎች ነበሩ፡፡

እንደ ጥምቀትና መስቀል ያሉ የከተራና የደመራ በዓላት በመጡ ቁጥር ሙስሊሞች መንገድ አጸዱ፤ እንደ ሮመዳን ያሉ በዓላት ሲመጡ ክርስቲያኖች እንዲህ አደረጉ ...» የሚሉ ዜናዎች ሲሰሩ በአንዳንድ ሰዎች የሚሰጡ አስተያየቶች አሉ፡፡ ለፖለቲካ ፍጆታ ነው፤ በመንግሥት ካድሬዎች ታዝዘው ነው፤ እንዲህ አድርጉ ተብሎ ነው ... እየተባለ ይወራል፡፡ እርግጥ ነው እንደዚያ ሊሆንም ይችላል፡፡ በመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ላይ ያሉ ባለሥልጣናት የሚያደርጉት አርዓያ ሆኖ ለመታየት፣ ምናልባትም ለፖለቲካ ፍጆታ ሊሆን ይችላል፡፡ እውነታው ግን በማህበረሰባችን ውስጥ ይህ ልማድ ያለ እና የነበረ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ የመንግሥት የሥራ ኃላፊ የአገሩ ሕዝብ የሚያደርገውን ነገር ቢያደርግ፣ የአገሩን ሕዝብ እሴቶች ቢያንፀባርቅ ምንም ችግር የለውም፡፡ ችግር የለውም ብቻ ሳይሆን ግዴታው ነው፡፡ ችግሩ ግን ለፖለቲካ ፍጆታ ተብለው የሚደረጉ ሌሎች ነገሮች ስላሉ እንዲህ አይነት በጎ ነገሮችን ጭምር በቅንነት እንዳይታዩ ያደርጋል፡፡ በዘመቻ የሚደረገውን እንተወውና እውነታው ግን በማህበረሰባችን ውስጥ ያለ መሆኑን ማወቅ ነው፡፡

ለምሳሌ የጥምቀት ዕለት የወደቀ የባንዲራ ምሰሶ እያነሱ ሲያቃኑ የነበሩት ሙስሊም አባት ማንም አዝዟቸው አይደለም፡፡ እየሄዱ የነበረው ብቻቸውን ነው። ማንንም ለማስደሰት ብለው አልነበረም፤ በአካባቢው ሰው የለም፡፡ ከታች እየመጣን የነበረውን ሁለት ሰዎች አይተው ይሆናል ብሎ መገመት በጣም የለየለት ጅልነት ይሆናል፡፡ ጭራሹንም ያዩን አይመስለኝም፡፡ አጠገባቸው ደርሰን፣ እርሳቸውም አቃንተው ጨርሰው ስንተላለፍ ነው ምናልባትም ልብ ብለውን ከሆነ፡፡ ያንን ሲያደርጉት የነበረው ለህሊናቸው ነው፡፡ ያ ባንዲራ የተሰቀለው ለበዓሉ ድምቀት መሆኑን ያምናሉ፤ ስለዚህ ወድቆ ሲያዩት አላስቻላቸውም ማለት ነው፡፡ ምን አገባኝ በሰው ሃይማኖት አላሉም ማለት ነው፡፡ በቅን ልቦና እና ህሊና ሲታሰብ እንዲህ ነው፡፡

አሁንም እደግመዋለሁ፤ ገጠመኙን ያነሳሁት ምንም የሚገርም ነገር ኖሮት አይደለም፡፡ ከፖለቲካ ውጭ ያለው የአገራችን የሕብረተሰብ ክፍል እየኖረው ያለው ሕይወት ነው፡፡ ይህን በማድረጋቸው መደነቃችንን ቢያውቁ ምናልባትም ሊስቁብን ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ለእነርሱ የዕለት ከዕለት ሕይወት ነው፡፡ አንድ ሰው መሰረታዊ ነገሮችን ማድረጉ የተፈጥሮ ግዴታ ነውና የሚደንቅ ነገር የለውም፤ እነርሱም ልክ እንደዚያ ነው የሚያዩት፡፡

ገጠመኙን ያነሳሁበት ምክንያት፤ እንዲህ አይነት ሃይማኖታዊ በዓላት ሲመጡ የሌላ እምነት ተከታይ የሆኑ ወገኖች እንዲህ አደረጉ የሚለው እንደ ትልቅ ዜና በመታየቱ ነው፡፡ ልክ ያልተደረገ ነገር፣ ወይም ሊደረግ የማይችል ነገር የተደረገ በማስመሰል ማዳነቅ ስህተት ይመስለኛል፡፡ በዚያ ልክ የማዳነቅ ሽፋን ሲሰጠው ነው ሰዎች ተጨማሪ ትርጉም ለመስጠት የሚገደዱት። እንዲህ ከሆነማ ሊያጸዱ የወጡት ሰዎች “‹እንዲህ አድርጉ› ተብለው ተገደው ነው ለሚል አተያይ ያጋልጣል፡፡ በአጭሩ የአንድ ሃይማኖት በዓላት ሲከበር የሌላኛው ሃይማኖት ተከታዮች ድጋፍ ማድረግና አብሮ ማክበር በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ውስጥ ያለ እና የሚኖሩበት ነው፡፡

እንዲህ አይነት ዜናዎችን ስመለከት ወደ ልጅነቴ እመለሳለሁ፡፡ ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ ሙስሊሞች በቁጥር ትንሽ ናቸው፡፡ አብዛኛው ኦርቶዶክስ ነው። ታዲያ ከሃይማኖታዊ በዓላት ይልቅ ሰርግ ሲደረግ የነበረው ነው ትዝ የሚለኝ፡፡ እንደ ልማድ ሆኖ ይሁን ሃይማኖታዊ አስተምህሮው ባይገባኝም ‹‹የሙስሊም እና የክርስቲያን ሥጋ›› የሚባል አለ፡፡ ሌላውን ምግብ አብረው እየበሉ የሥጋ አይነት ሲሆን ይለያያል፡፡ ማረድ ያለበትም የእምነቱ ተከታይ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

በዚህ ሁኔታ ሰርግ ሲደረግ፤ እንደ ባለ ሰርጉ አቅም ሁለትና ከዚያ በላይ ነው የሚታረደው፡፡ ሁለት ግን ግዴታ ነበር፡፡ አለበለዚያ እርድ የሌለበት ሰርግ (በፆም ምግቦች) ይደረጋል እንጂ አንድ ብቻ ሊታረድ አይችልም። የቻለ ሁለት ከብት፣ ያልቻለ ሁለት ፍየል ነው ሊያርድ የሚችለው፡፡ አንዱን ክርስቲያን ያርዳል፣ አንዱን ሙስሊም ያርዳል፡፡ በተለያየ ድስት ይሰራል። ሙስሊም ከሙስሊሙ፣ ክርስቲያን ከክርስቲያኑ ይበላሉ ማለት ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ አስተናጋጅ ተሳስቶ ከአንዱ ሃይማኖት ለሌላኛው ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህኔ ‹‹ኸረ ይሄኛው የሙስሊም ነበር›› ወይም ‹‹ኸረ ይሄኛው የክርስቲያን ነበር›› ይባላል፡፡ ይሄኔ በቀልድ እያዋዙ ‹‹ባክህ ሁለቱም ከሰኞ ገበያ ነው የተገዙት›› በማለት በሬዎች የተገዙበትን ሰኞ ገበያ የምትባል የአካባቢያችንን ገበያ ይጠቅሳሉ፡፡ አንድ አይነት በሬ ወይም ፍየል ናቸው፤ ምንም ልዩነት የለውም ማለታቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል በሬው ወይም ፍየሏ ሃይማኖት የሌላቸው ፍጡር ስለሆኑ ምንም ልዩነት የለውም እያሉ ፍልስፍና አከል ጨዋታዎችን ይጫወታሉ።

እንግዲህ እነዚህን ሰዎች ‹‹ሙስሊምና ክርስቲያን እኮ አንድ ነው›› ብለን ብንነግራቸው ‹‹እና ታዲያ ድሮስ ስንት ሊሆኑ ነበር?›› በማለት ነው የሚስቁብን። ለእነርሱ ዜና አይደለም ማለት ነው፡፡ ‹‹ሙስሊምና ክርስቲያን እኮ ተከባብሮ ነው የሚኖር›› ብንላቸው ‹‹እና ታዲያ ከመከባበር ውጭ ምን ሊሆን ነበር?›› ብለው ነው የሚመልሱልን፡፡ ወይም ‹‹አንተ ነህ እሱን የምትነግረኝ?›› ብለው ሊገረሙብን ይችላሉ፡፡

በተለይም እንዲህ እንደ ጥምቀት ያሉ በዓላት ደግሞ እንዲህ አይነት ማህበራዊ እሴቶችን አጉልተው ያሳያሉና እውነተኛውን የማህበረሰብ መስተጋብር እናይባቸዋለን፡፡

## ነፃ ሃሳብ

# ትኩረት የዲጂታል ኢትዮጵያን...

ከገጽ 5 የዞረ

ብዙ ዘርፎችን ቢጎዳም፣ ይህ ዘርፍ ግን ትርፋማ የሆነበት ሁኔታ ነው የታየው፡፡

አሁን ደግሞ እያንዳንዱ ዜጋ ከቴክኖሎጂው ውጪ መሆን የማይችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በሶስተኛ ወገን በኩልም ቢሆን ቴክኖሎጂውን መጠቀሙ የግድ ሆኗል። ገንዘብ የግድ ሊባል በሚችል መልኩ እየተንቀሳቀሰ ያለው በዲጂታል ስርዓቱ በኩል መሆኑ ይህን ሁኔታ የግድ ያደርገዋል፡፡ ጉዳይ ለመፈጸም የትኛውም መስሪያ ቤት የሄደ አገልግሎቱን የሚያገኘው በዲጂታል መንገድ መሆኑም እንደዚያው ነው፡፡

ተማሪዎች በቴሌግራምና በመሳሰሉት መጻህፍት፣ የቤት ስራ፣ ወዘተ እንዲደርሳቸው እየተደረገ ነው። እነዚህ የዘርፉ አገልግሎቶች ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡

ቴክኖሎጂው በዚህ ልክ ማገልገል የቻለው ብዙ ኢንቨስት ተደርጎበት ነው፡ ቴክኖሎጂው ከዚህም በላይ እንዲያገለግል ይፈለጋል፤ ለእዚህም ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል፡፡ ይህን አገልግሎት መሰጠቱን በአግባቡ እንዲወጣ የሚያስችል መሰረተ ልማትና በርካታ ከቴክኖሎጂው ጋር የሚሄዱ አቅርቦቶችን ዝግጁ ማድረግ ላይም በትኩረት መሰራት ይኖርበታል፡፡

በቴክኖሎጂው ብዙ ለመስራት የታሰበ ቢሆንም፣ ይህን የሚያሰራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በኩል ተከታታይነት ያለው ስራ እየተሰራ ነው ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ የኔት ወርክ መጨናነቅ የሀገሪቱ መሰረታዊ ችግር ሆኖ መቀጠሉም ይህንኑ ይጠቁማል። በየተሄደበት ተቋም በኔትወርክ መጨናነቅ ሳቢያ ጉዳይ የሚዘገይበት፣ የሚያድርበት ሁኔታ በስፋት እየታየ ነው፡፡

በኔትወርክ መጨናነቅ ሳቢያ አጭር የጽሁፍ መልዕክት ማግኘት የማይችልበት ሁኔታም ጥቂት ተብሎ የሚታይ አይደለም፡፡ በዚሁ የክፍያ ስርዓት በኔትወርክ ችግር ሳቢያ ሰዎች ገንዘባቸውን ማንቀሳቀስ እየተቸገሩ ያለበት ሁኔታም ሌላው የዘርፉ ደንቃራ ሲሆን ይስተዋላል፡፡

ገንዘብ ሲወጣና ሲገባ ለደንበኞች መተላለፍ ያለባቸው አጭር መልዕክቶች በወቅቱ ለደንበኞች አይለቀቁም፡፡ በእዚህ በኩል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስም በጥሩ አይነሳም፡፡ አጭር የጽሁፍ መልዕክት ማለት ደረሰኝ ነው፡፡ ገንዘብ በወጣ በገባ ቁጥር ወዲያውኑ የጽሁፍ መልዕክት የማይደርስ ከሆነ ችግሩ በእርግጥም አሳሳቢ ነው፡፡

ይህ በዋና ዋና ከተሞች  በስፋት የሚታይ ችግር ወደ ገጠራቱ የሀገሪቱ ከተሞች ሲደርስ ምን ያህል የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ይህ ደግሞ ዲጂታል ኢትዮጵያን እአአ በ2025 እውን ለማድረግ ደንቃራ ይሆናል፡፡

ቴክኖሎጂውን እንዲሁም በቴክኖሎጂው የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚጠየቀው ገንዘብ ከፍተኛ እየሆነ መምጣትም ሌላው የዲጂታል ዘርፍ ፈተና ነው። አሁን ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠየቀው ክፍያ በእያንዳንዱ ግለሰብ ደረጃ ከፍተኛ መጠን ያለው በጀት መያዝን የሚጠይቅ ሆኗል፡፡

ለዳታ የሚደረግ ክፍያ ከፍተኛነት ሌላው ደንቃራ ነው፡፡  በጠራራ ጸሀይ በዳታ እንደ ልብ መገናኘት አይቻልም፤ በእዚህ ሳቢያ ገባ ወጣ ማለት የአብዛኛዎቹ የቴክኖሎጂው ተጠቃሚዎች ኢትዮጵያውያን ፈተና እየሆነ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ መረጃዎችን በወቅቱ እንዳያገኙ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

በተለይ ለሞባይል ስልክ አገልግሎት የሚወጣው ወጪም እየበዛ መጥቷል፤ አሁን ካርድ ተሞልቶ አሁን ያልቃል፡፡ እነዚህ ወጪዎች እንግዲህ ተራ አገልግሎት ለማግኘት ሲባል የሚወጡ ናቸው፡፡ የሚፈለገው አገልግሎት እየጨመረ ሲሄድ ክፍያውም በዚያው ልክ እየጨመረ ይሄዳል፡፡

ገንዘብ ሲንቀሳቀስ የሚከፈለው ክፍያ በዚህች ሀገር አዲስ ነው፤ በእርግጥ ገንዘቡን ባንክ ሄዶ ለማውጣት በሚደረግ እንቅስቃሴ ሊወጣ የሚችለው የትራንስፖርት ወጪ እና ገንዘቡን ለማውጣት የሚደርስ እንግልትን

**ቴክኖሎጂው በዚህ ልክ ማገልገል የቻለው ብዙ ኢንቨስት ተደርጎበት ነው ቴክኖሎጂው ከዚህም በላይ እንዲያገለግል ይፈለጋል፤ ለእዚህም ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል፡፡ ይህን አገልግሎት መሰጠቱን በአግባቡ እንዲወጣ የሚያስችል መሰረተ ልማትና በርካታ ከቴክኖሎጂው ጋር የሚሄዱ አቅርቦቶችን ዝግጁ ማድረግ ላይም በትኩረት መሰራት ይኖርበታል**

በማስቀረት ወዘተ. ሊካካስ ይችል ይሆናል፤ ይህ ተጠቃሚነት አለ ተብሎ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ መጠየቅ ተገቢ አይደለም፡፡

የሚፈጸመው ክፍያ ብዙ አይነት ነው፤ ሁሉም ገንዘብ ይፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ የአብዛኛው ማህበረሰብ ገቢ ዝቅተኛ ለሆነባት ኢትዮጵያ ሕዝብ ፈታኝ አይሆንም ተብሎ አይታሰብም፡፡

በሀገሪቱ እየተጠየቀ ያለውን ክፍያ በሌሎች ሀገሮች ከሚጠየቅ ክፍያ ጋር እያነጻጸሩ የሚተቹ እንደነበሩም አውቃለሁ፡፡ የክፍያው እየበዛ መምጣት አስመልክቶ ለሚመለከተው አካል ቅሬታ ሲቀርብ ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው ምላሽ ክፍያው እየበዛ የመጣው ለመሰረተ ልማቱ ማስፋፊያ ሲባል ነው ይባል ነበር፡፡ መሰረተ ልማት የማስፋፋቱ ስራ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮቴሌኮም ትከሻ ላይ የወደቀ ነበር፤ አሁን ተገዳዳሪ ኩባንያ ወደ ሀገሪቱ ገብቶ እየሰራ ነው፡፡ ሌሎችም ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። ያኔ የተረጋጋ ክፍያ ሊኖር ይችላል ብለን እናስብ፤ እዚያው ድረስ ግን ክፍያው እየናረ እንዳይሄድ ማድረግ ላይ ቢሰራ መልካም ነው እላለሁ፡፡

በዲጂታል ቴክኖሎጂ ብዙ እንደሚሰራ ይጠበቃል፡፡ ለእዚህ ደግሞ መሰረተ ልማት ማስፋፋት ላይ በስፋት መስራቱ አንድ ነገር ሆኖ ዜጎች በሚገባ እንዲጠቀሙበት ማድረግ ላይም መስራት የግድ ይሆናል፡፡ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እየተከናወነ ያለው ተግባር በሚፈለገው መልኩ ስኬታማ እንዲሆን አሁንም፣ በቀጣይም ለአቅም ግንባታ ስራዎች ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የቴክኖሎጂው ቁሳቁስ ዋጋ ውድነትና እንደ ልብ አለመገኘት ሌላው ትልቁ ተግዳሮት ነው፡፡ በዚህች ሀገር በቴክኖሎጂው ብዙ መስራት እየተፈለገ፣ ለእዚህ ደግሞ እንደ ስማርት ስልክ ያሉት ወሳኝ መሆናቸው እየታወቀ እነዚህ ቁሶች በመንግስት በኩል አሁንም የቅንጦት እቃዎች ተደርገው እየታዩ ናቸው፡፡

የእነዚህ ቁሶች የቅንጦት እቃነት ጊዜው አልፎበታል፡፡ ይህን ችግር የዘርፉ ባለሙያዎች በእጅጉ እየተቹት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ቁሶች ከፍተኛ ገንዘብ እየተጠየቀባቸው እየተቀረጡ እንዲገቡ ማድረግ ዜጎች በዲጂታል ቴክኖሎጂው ብዙ ርቀት እንዳይጓዙ እንደሚያደርግ ጥርጥር የለውም፤ ዜጎች ብቻ አይደለም የሚጎዱት፤ ስራዎች ሁሉ በቴክኖሎጂው እንዲከናወኑ እየሰራ ባለው መንግስት እቅድ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ያሳርፋል፡፡ ከዚህ አኳያ ኢትዮ ቴሌኮምና ሳፋሪ ኮም አንዳንዴ እነዚህን ቁሶች በዝቅተኛ ዋጋ እያቀረቡ ያለበት ሁኔታ ሊበረታታ ይገባዋል፡፡ አቅርቦቱ ግን ከዚህም በላይ መሆን ይኖርበታል፡፡

ታብሌቶች፣ ላብቶፖችና ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮችም እንዲሁ የማግኘት ችግር አለ። እነዚህ ተቋማት ለተማሪዎች፣ ለመምህራን፣ ለተቋማት ሰራተኞች፣ ወዘተ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፤ ቁሳቁሱ ከእነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ዜጋም በሚያስፈልጉበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡

እነዚህን ቁሳቁስ ምንም አይነት ይሁኑ ምንም አይነት፣ ለዜጎች የሚዳረሱበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡  እነዚህን አለማስፋፋት ሰራዎች በዲጂታል ቴክኖሎጂ በሚከናወኑበት ፍጥነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳርፋል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ወይም የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሀይምናን የሚያበራክትም ነው የሚሆነው፡፡

እነዚህን ቁሳቁስ በእርዳታም፣ በአነስተኛ ዋጋ ግዥም ሆነ በሌላም በሌላም መንገድ ዜጎች የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር አይደለም፡፡ ቢያንስ ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች እንደልብ ሊገኙ የሚችሉባቸውን እንደ ላይብራሪ ያሉ ተቋማትን በቅርብ ርቀት ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

ይህ ሲሆን ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች ማግኘት ይችላሉ፤ በዚህም ትምህርት ቤት ያገኙትን እውቀት በአካባቢያቸው በሚያገኟቸው በእነዚህ ቁሳቁስ ማዳበር ይችላሉ፡፡ ከቴክኖሎጂው ጋር የበለጠ ቤተሰብ እየሆኑ መጥተው የዲጂታል ኢትዮጵያ ማህበረሰብ መሆን ይችላሉ፡፡

የዘርፉ ቴክኖሎጂዎች እንደልብ አለመገኘት የዘርፉ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ከተመረቁ በኋላ ከቴክኖሎጂው እንዲርቁ እያደረጋቸው ነው። ተመራቂዎቹ ሶፍትዌሮችን ያለሟሉ ሲባሉ፣ ለዘርፉ ብዙ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ተብለው ሲታሰቡ በቁሳቁሱ እጥረት ሳቢያ ከተመረቁበት ሙያ ውጭ ሌላ መስክ ላይ እየተሰማሩ ናቸው፡፡ ይህ ትልቅ እጦት ነው።

ቁሳቁሱን ማግኘት አንድ ነገር ሆኖ በቁሳቁሱ ለመገልገል የሚያስችሉ የዋይፋይና የመሳሰሉት አቅርቦቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኙበት ሁኔታም መፈጠር ይኖርበታል፡፡ ይህ ደግሞ ለይስሙላ መሆን የለበትም፡፡ በሚገባ መገልገል የሚያስችል የኔትወርቅ አቅምም አብሮ ሊኖር ይገባል፡፡

የዘርፉን ቴክኖሎጂዎች ማግኘት እንደ መሰረታዊ መብት መቆጠር ይኖርበታል፡፡ ሁሉንም አገልግሎት በዲጂታል ስርዓት ለመፈጸም የወሰነና ወደ ስራ የገባ መንግስት በአነዚህ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት እጥረት ስሙ መነሳት የለበትም፡፡ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት በእርዳታም፣ ልዩ በጀት በመመደብም ቢሆን ዜጎች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት፣ ቴክኖሎጂዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የቅንጦት እቃ በሚል የሚጠይቅባቸውን ታክስም መልሶ ቢመለከተው ጥሩ ይሆናል፡፡

አሁን በስራ ላይ ያሉት በየተቋማቱ የሚገኙ የቴክኖሎጂው ውጤቶች ዘመኑን የዋጁ አይደሉም። በአንዳንድ ተቋማት አሉ የሚባሉት ኮምፒውተሮች ዘመን ያለፈባቸው ናቸው፤ ዳታ ለማውጣት፣ ፕሮሰስ ለማድረግ ሴቭ ለማድረግ ለመክፈትም ሆነ ለመዝጋት በእጅጉ የደከሙ ልብ አድክሞች ናቸው፡፡ እነዚህንም ዘመኑን በዋጁ ኮምፒውተሮች መተካት ድረስ የዘለቀ ተግባር ማከናወን ይገባል፡፡

ቴክኖሎጂዎቹን ከውጭ እየገዙ ማሟላት ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ቴክኖሎጂዎቹን በሀገር ውስጥ መገጣጠምና ማልማት ላይም መስራት ያስፈልጋል። በቅርቡ አንድ መንግስታዊ የልማት ተቋም ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን የትራክተር እና ኮምባይነር ብዛት በግዥ ማሟላት እንደማይቻል በማመን በእነዚህ የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች መገጣጠምና ማምረት ላይ በስፋት እንደሚሰራ ማስታወቁን አስታውሳለሁ፡፡

በዲጂታል ዘርፉ ላይ የሚሰሩት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና የመሳሰሉት መንግስታዊ ተቋማትና የግሉም ዘርፍ የዚህን ተቋም እርምጃ በአርአያነት በመውሰድ መተግበር ይኖርባቸዋል። የዚህች ሀገር የዲጂታል ቴክኖሎጂ ልማት ግብ ሰፊ መሆን ይህንን ማድረግም ይጠይቃል፡፡

ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት ከአፍሪካ ሀገሮች ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች፤ በፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት በኩል ግን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው የምትገኘው፡፡ የዚህ አንዱ ምክንያት በዲጂታል ቴክኖሎጂ በኩል ብዙ ርቀት አለመጓዟ ነው፡፡ መንግስት ይህን ለመቀየር እየሰራ ነው፡፡ መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ ብሄራዊ ባንክ እአአ በ2025 የሀገሪቱን ዜጎች የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት 70 በመቶ ለማድረስ ግብ ጥሎ እየሰራ ነው፡፡

በእዚህ ልክ የሚሰራ መንግስት፣ ለእዚህ እውን መሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በሚያደርጉ እንደ ስማርት ስልክ፣ ታብሌት፣ ላፕቶፕና ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች ያሉትን ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግም በትኩረት መስራት ይኖርበታል፡፡ በእነዚህ ቁሳቁስ ላይ መስራት በሀገሪቱ በሰው ሰራሽ አስተውሎት/አርተፊሻል ኢንተለጀንስ /ላይ በስፋት ለመስራት ለተያዘውም እቅድ ስኬት ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ፓኪስታንና ኢራንን ውጥረት ውስጥ የከተተው ጉዳይ

በጋዜጣው ሪፖርተር



ከቀናት በፊት ፓኪስታን በኢራን የሚገኙ ታጣቂዎችን ዒላማ ያደረጉ የአየር ጥቃቶችን መፈጸሟን ተከትሎ ዘጠኝ ሰዎች ተገድለው ነበር።

ጥቃቱን በተመለከተ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብዙ ጥናት የተደረገበት በኢራን የታጣቂዎች መደበቂያ የሆነ ቦታ ነው ዒላማ የተደረገው ብሏል።

ከዚህ የአየር ጥቃት በኋላ ኢራን በተራዋ በፓኪስታን የመሸጉ ናቸው ያለቻቸውን ታጣቂዎች ዒላማ አድርጋ የአየር ጥቃት ፈጽማለች። በዚህ ጥቃት ሁለት ሕጻናት መገደላቸውን የፓኪስታን መንግሥት አስታውቋል።

ሁለቱም መንግሥታት በእነዚህ ጥቃቶች ደስተኞች አይደሉም። ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውንም እስከማቋረጥ ደርሰው ነበር።

ፓኪስታን በኢራን ተደብቀው ይገኛሉ በምትላቸው ተገንጣይ ቡድኖች ላይ የሚሳኤል ጥቃት ፈጽማለች። ኢራን ደግሞ በፓኪስታን መቀመጫውን ባደረገው የሱኒ ታጣቂ የሆነው ጃኢሽ አል-አደለ የተባለውን ቡድን ዒላማ አድርጋለች።

የፓኪስታን መንግሥት በአገሩ ውስጥ የሽብር ተግባራትን ፈጽመዋል ያላቸውን የባሎቺስታን ነፃነት ሠራዊት እና የባሎቺስታን ነፃነት ግንባር ኢራን ውስጥ መምታቱን ይገልጻል።

የፓኪስታን ጦር እነዚህን ሁለት ቡድኖች ለመምታት ሰው አልባ አውሮፕላኖች፣ ሮኬቶች፣ ሚሳኤሎች እና ሌሎች መሣሪያዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይገልጻል።

ጥቃቱ የተፈጸመበት ኢራን እና ፓኪስታን ድንበር ላይ የምትገኘው አዋሳኟ የኢራን ከተማ ሳራቫን አቅራቢያ ነው። ለበርካታ አስርተ ዓመታት በፓኪስታኗ ባሎቺስታን ግዛት በርካታ ተገንጣይ ኃይሎች የትጥቅ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ቆይተዋል።

እነዚህ ቡድኖች በፓኪስታን ጦር እና ፖሊስ ላይ ተደጋጋሚ ጥቃቶችም ሲፈጽሙ ቆይተዋል። ከተገንጣይ ቡድኖቹ መካከል ጠንካራዎቹ የባሎቺስታን ነፃነት ሠራዊት እና የባሎቺስታን ነፃነት ግንባር ናቸው።

የፓኪስታን ባለሥልጣናት የእነዚህ አማጺያን ቡድኖች አባላት በኢራን ተሸሽገው እንዲኖሩ ተፈቅዶላቸዋል በማለት ቴህራንን ይከሳሉ።

ኢራን በበኩሏ በመንግሥቷ ላይ ነፍጥ ያነሳውን ጃኢሻ አል-አደለ (የፍትሕ እና ነፃነት ሠራዊት) ቡድንን ለመምታት ነበር በፓኪስታን ግዛት ውስጥ የአየር ጥቃት የፈጸመችው።

ይህ ቡድን የብዙኃን ሺዓዎች ሀገር በሆነችው ኢራን ለሚኖሩ ሱኒዎች የመብት ተሟጋች ነኝ ሲል እራሱን ይገልጻል። ሺዓ ሙስሊሞች በሚበዙባት ኢራን ይህ ቡድን በርካታ ጥቃቶች በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ላይ በመፈጸም ክስ ይቀርብበታል።

ጃኢሻ አል-አደለ እ.አ.አ. በ2005 ላይ በወቅቱ የኢራን ፕሬዚዳንት ሞሐመድ አሕመዲነጃድ ላይ ያልተሳካ ጥቃት ፈጽሞ ነበር።

ኢራን ጃኢሽ አል-አደለ የአሜሪካ እና የእስራኤል ድጋፍ አለው ስትል ትከሳለች። በዋሽንግተን የኒው ላይንስ ኢንስቲትዩት ኦፍ ስትራቴጂ ኤንደ ፖሊስ ባልደረባ የሆኑት ዶ/ር ካምራን ቡካህሪ ደግሞ ፓኪስታን ለኢራን ጥቃት ምላሽ የሰጠችው ቴህራን ኢራቅ ላይ እንዳደረገችው ደጋግማ የአየር ጥቃት እንዳትፈጽም ነው ይላሉ።

ባለሙያው በኢራን እና በፓኪስታን አዋሳኝ የድንበር አካባቢዎች የተሰባሰቡ ቡድኖች ለሁለቱም ሀገራት ችግር ፈጣሪ ሆነው ቆይተዋል ይላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ኢራን ዒላማ ያደረገችው ቡድን በፓኪስታን ዘንድም እንደ ጠላት የሚታይ ነው።

ፓኪስታናዊው ጋዜጠኛ እና ተንታኝ ባቂር ሳጃድ ምንም እንኳ አሁን ላይ የአየር ጥቃቶች ቆመው ሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን መልሰው ቢያስቀጥሉም፣ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ውጥረት መቀጠሉ አይቀሬ ነው ሲል ገልጿል።

“በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ውጥረት ድንገት ይቀንሳል ማለት አይደለም። በሀገራቱ መካከል ያለው አለመተማመን በአማጺያኑ ተደጋጋሚ ጥቃት ተጋግሎ በቀጣናው ያለውን የደኅንነት ስጋት ከፍ ያደርገዋል” ይላል።

በአካባቢው የነገሰውን ውጥረት ለማርገብ በርካታ አካላት ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛል። በተለይ እስራኤልና ሐማስ ከፍተኛ ግጭት ውስጥ በገቡበት ወቅት በተጨማሪ ኢራንና ፓኪስታን ደም አፋሳሽ ጦርነት ውስጥ የሚገቡ ከሆኑ ለዓለም ኢኮኖሚ ዕድገት እንቅፋት እንደሚሆን ባለሙያዎች ሃሳብ እየሰጡ ይገኛል።


# ስፖርት





ብርሃን ፈይሳ




በጠንካራ ፉክክር የታጀበውና ለመገመት አዳጋች ሆኖ የቀጠለው የዘንድሮው የአፍሪካ ዋንጫ መካሄድ ከጀመረ ዛሬ 10ኛ ቀኑን አስቆጥሯል። ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት የተሰጣቸው ሀገራት ነጥብ በመጣል የምድብ ጨዋታዎቹን አጓጊ አድርገው የቀጠሉ ሲሆን፤ 16ቱን የሚቀላቀሉ የመጀመሪያዎቹ አራት ሀገራት በዛሬው ጨዋታ ይለያሉ፡፡

በስድስት ምድብ ተከፍለው እየተጫወቱ የሚገኙት 24 ቡድኖች መካከል ቀጣዩን ዙር መቀላቀል የሚችሉት ፍንጭ እየታየ ቢሆንም፤ እስካሁን ከተመዘገበው ውጤት አንጻር ከምድብ አንድ እና ምድብ ሁለት አላፊ የሚሆኑትን ቡድኖች በትክክል ለመገመት ግን አዳጋች ሆኗል፡፡ በመጀመሪያው ምድብ ከናይጄሪያ ጋር በእኩል ብትለያይም ጊኒ ቢሳውን 4ለ2 በሆነ ውጤት ማሸነፏ የሚታወስ ነው። በዚህ ጨዋታ ላይ ከተቆጠሩት ግቦች መካከልም ሦስቱን ከመረብ በማገናኘት ሀትሪክ መሥራት የቻለው 34 ዓመቱ የኢኳቶሪያል ጊኒ ተጫዋች ኢሚሊዮ ኒሱን ነው፡፡

ዛሬ አቢጃን በሚገኘው የኮትዲቯራውያን ብሔራዊ ስታዲየም አላሳኔ ኦታራ ኢኳቶሪያል ጊኒ 16ቱን የመቀላቀል እድሏን የምታረጋግጥበትን ጨዋታ ከውድድሩ አዘጋጅ ኮትዲቯር ጋር ታከናውናለች። በተፎካካሪነታቸው ጥሩ ከሚባሉ ቡድኖች አንዱ የሆነው ኢኳቶሪያል ጊኒ አራት ነጥብ በማስመዝገብ ከደረጃው አናት መቀመጥ ችሏል፡፡ ጅማሬውን በጊኒ ቢሳው ላይ 2 ለባዶ በሆነ የበላይነት ያደረገው የኮትዲቯር ብሔራዊ ቡድን በናይጄሪያ የደረሰበት የ1 ለምንም ሽንፈት ወደ ሦስተኛ ደረጃ እንዲወርድ አድርጎታል፡፡ ይሁንና በዛሬው ጨዋታ ነጥብ ማስመዝገብ ከቻለ ቀጣዩን ዙር የመቀላቀል እድሉን የሚያለመልም በመሆኑ የሁለቱ ቡድኖች ጨዋታ አጓጊ ሊሆን ችሏል፡፡

በምድቧ የተሻለ ተፎካካሪ ሆና የቀረበችው ኢኳቶሪያል ጊኒ የፈተነቻቸው ናይጄሪያዎች በኮትዲቯር ላይ የተቀዳጁት ነጥብ ወደ ቀጣዩ ዙር አንድ እግራቸውን እንዲያስገቡ ያደረጋቸው ሆኗል። በጨዋታው ዝሆኖቹን አሸናፊ ያደረጋቸው ብቸኛ ግብም ዊሊያም ተሩስት በ55ኛው ደቂቃ በፍጹም ቅጣት ምት ያስቆጠረው ነው። የዛሬው የምድቡ የመጨረሻ ጨዋታም በተደጋጋሚ ሽንፈት ወደ ሀገሯ የመመለሷን ነገር ካረጋገጠችው ጊኒ ቢሳው ጋር ያገናኛቸዋል፡፡ በእርግጥ ዝሆኖቹ ጨዋታውን በአሸናፊነት፣ አሊያም በእኩል ማጠናቀቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ የኮትዲቯርና ኢኳቶሪያል ጊኒ ውጤት ደግሞ ቀጣዩን ጉዞ በግልጽ የሚያመላክት ይሆናል፡፡

በምድብ ሁለት ተጠባቂዋ ግብፅ ሁለቱን ጨዋታዎች በእኩል ነጥብ መጨረሷን ተከትሎ በሁለት ነጥብ ከደረጃ ሰንጠረዡ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች፡፡ በዛሬው መርሐ ግብርም ምድቡን ስትመራ ከቆየችው ኬፕቨርዴ ጋር ይጫወታሉ። ፈርዖኖቹ በሞዛምቢክ ተፈትነው ቀጣዩን ጨዋታ ከጋና ጋር ቢያደርጉም፤ ከባድ ሚዛን በተባለለት በዚህ ጨዋታም በተመሳሳይ በእኩል ነጥብ ነበር የፈጸሙት። የጋናን ሁለት ግቦች ሞሐመድ ኩዱስ ከመረብ ሲያሳርፍ የግብፅን የአቻነት ግቦች ደግሞ ሙስጠፋ ሞሐመድ እና ማራሙሽ በ69ኛው እና 74ኛው ደቂቃ ላይ ነበር ያስቆጠሩት። የግብፃውያኑ ቁልፍ ተጫዋች ሞሐመድ ሳላህ ደግሞ ጉዳት አስተናግዷል። ለሰባት ጊዜያት የአፍሪካ ዋንጫን በማንሳት ቀዳሚ የሆነችው ግብፅ አሁንም ለሻምፒዮናነት ትጠበቅ እንጂ ዋንጫውን ካነሳች ግን 14 ዓመታት ተቆጥረዋል። የአፍሪካው ጠንካራ ቡድን ዛሬ ከኬፕቨርዴ ጋር በሚኖረው ወሳኝ ጨዋታ ተጠባቂውን ብቃት በማሳየት 16ቱን ቡድኖች እንደሚቀላቀል ይጠበቃል።

የአፍሪካ ዋንጫውን በኬፕቨርዴ የ2 ለ1 ሽንፈት የደረሰባቸው ጥቋቁሮቹ ከዋክብት በቀጣዩ ጨዋታ ከግብፅ ጋር በእኩል ነጥብ በመለያየት አንድ ነጥብ ብቻ በማስቆጠር በደረጃ ሰንጠረዡ መጨረሻ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ ለዋንጫ ሲገመት ባልተጠበቀ ሁኔታ የተገኘው ቡድኑ ወደ ቀጣዩ ዙር የማለፍ እድሉ አጠራጣሪ ሆኖ ዛሬ ከሞዛምቢክ ጋር ይጫወታል። ደቡብ አፍሪካዊቷ ሀገር ሞዛምቢክም የማለፍ እድሏ አጠራጣሪ ሆኖ ጨዋታውን ታከናውናለች።